www.abyssinialaw.com

# የተሻሻለው የወንጀል ቅጣት

# አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006

## ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ጥቅምት 1 ቀን 2006 ዓ.ም

<u>አዲስ አበባ</u>

www.abyssinialaw.com

# ማውጫ


| የተሻሻለው የወንጀል ቅጣት<br>አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006<br>ክፍል አንድ<br>ጠቅላላ ድንጋጌዎች | | |
|---|---|---|
| አንቀጽ/አባሪ | ርዕስ | ገጽ |
| 1 | ስያሜ | 9 |
| 2 | ትርጓሜ | 9 |
| 3 | የመመሪያው ዓላማና ግብ | 9 |
| 4 | መሠረታዊ ድንጋጌዎች | 10 |
| ክፍል ሁለት<br>ነፃነትንና ሕይወትን የሚያሳጡ ቅጣቶችና የገንዘብ መቀጮ ሠንጠረዥ | | |
| 5 | የቅጣት እርከኖች ሠንጠረዥ | 12 |
| 6 | ነጻነትንና ሕይወትን የሚያሳጡ ቅጣቶች እርከን ሠንጠረዥ | 12 |
| 7 | የገንዘብ መቀጮ ሠንጠረዥ | 13 |

www.abyssinialaw.com


| | | |
|---|---|---|
| ክፍል ሦስት<br>የወንጀል መነሻ ቅጣት ስለሚወሰንበት ሁኔታ<br>ንዑስ ክፍል አንድ<br>እንደ ወንጀሉ ክብደት ደረጃ የወጣላቸው የወንጀል ዓይነቶች<br>ድንጋጌዎች እና የወንጀል ደረጃዎች<br>ርዕስ አንድ<br>በመንግስት ላይ የሚደረጉ ወንጀሎች | | |
| 8 | የአገሪቱን የፖለቲካና የግዛት አንድነት በመንካት የሚደረግ ወንጀል (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 241) | 14 |
| 9 | መገፋፋትና ግዙፍ ያልሆነ የማሰናዳት ተግባር (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 257) | 16 |
| ርዕስ ሁለት<br>በታወቁ ገንዘቦች፣ የግዴታ ወይም የዋስትና ሰነዶች፣ ማህተሞች፣ ቴምብሮች ወይም መሳሪያዎች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች | | |
| 10 | የሐሰት ገንዘብ፣ የግዴታ ወይም ዋስትና ሰነዶች(የወንጀል ሕግ አንቀጽ 356-362) | 20 |
| ርዕስ ሦስት<br>በመንግስት ሥራ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች | | |
| 11 | በሥልጣን ያለአግባብ መገልገል (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 407) | 32 |

www.abyssinialaw.com

| | | |
|---|---|---|
| ርዕስ አራት<br>በሰው ሕይወት፣ አካልና ጤንነት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች<br>ምዕራፍ አንድ<br>በሰው ሕይወት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች | | |
| 12 | በሰው ሕይወት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 539-543) | 37 |
| ምዕራፍ ሁለት<br>በሰው አካልና ጤንነት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች | | |
| 13 | በሰው አካልና ጤንነት ላይ የሚፈጸም ወንጀል (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 555-560) | 46 |
| ርዕስ አምስት<br>በሰው ነጻነት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች | | |
| 14 | በሕገ ወጥ መንገድ ኢትዮጵያውያንን ወደ ውጪ ሀገር መላክ (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 598) | 55 |
| ርዕስ ስድስት<br>በመልካም ጸባይ እና በቤተዘመድ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች | | |
| 15 | በግብረ ሥጋ ነጻነትና ንፅህና ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 620-628) | 59 |

www.abyssinialaw.com


| | | |
|---|---|---|
| ርዕስ ሰባት<br>በንብረት መብቶች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች | | |
| 16 | የስርቆት ወንጀሎች (የወንጀል ህግ አንቀጽ 665 እና 669) | 85 |
| 17 | የውንብድና ወንጀሎች (የወንጀል ህግ አንቀጽ 670 እና 671) | 90 |
| 18 | የማታለል ወንጀሎች (የወንጀል ህግ አንቀጽ 692 እና 693) | 98 |
| ንኡስ ክፍል ሁለት<br>ደረጃ ላልወጣላቸው ወንጀሎች በቅጣት ማንዋሉ መሠረት ስለሚሰራበት ሁኔታ | | |
| 19 | ደረጃ ያልወጣላቸው ወንጀሎች የወንጀል ደረጃና የቅጣት መነሻ እርከን አወሳሰን | 101 |
| 20 | ቅጣቱ በወንጀል ሕግ ተለይቶ በሚታወቅበት ጊዜ ስለቅጣት አወሳሰን | 104 |
| ክፍል አራት<br>የቅጣት ማክበጃና ማቅለያዎችን ስለ ማስላት<br>ንዑስ ክፍል አንድ<br>የቅጣት ማክበጃዎችን ስለ ማስላት | | |
| 21 | ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች በሚኖሩበት ጊዜ ቅጣቱ ስለሚከብድበት አሰራር | 105 |

www.abyssinialaw.com


| | | |
|---|---|---|
| 22 | ልዩ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች በሚኖሩ ጊዜ ቅጣቱ ስለሚከብድበት አሰራር | 106 |
| ንዑስ ክፍል ሁለት<br>የቅጣት ማቅለያዎችን ስለ ማስላት | | |
| 23 | ጠቅላላ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች በሚኖሩበት ጊዜ ስለሚኖረው አሰራር | 107 |
| 24 | ልዩ የቅጣት ማቅለያዎች | 108 |
| 25 | በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 86 መሰረት የቅጣት ማክበጃና ማቅለያዎች በሚኖሩ ጊዜ ስለሚሰላበት ሁኔታ | 108 |
| ክፍል አምስት<br>የቅጣት አሰላል ሥነ ሥርዓት | | |
| 26 | የቅጣት አሰላል ሥነ ሥርዓት ቅደም ተከተል | 108 |
| ክፍል ስድስት<br>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች | | |
| 27 | ከዚህ መመሪያ ውጪ ቅጣት ሊወሰን የሚችልበት ሥርዓት | 110 |
| 28 | የንብረት ግምት መወሰንን በተመለከተ | 110 |
| 29 | ስለቅጣት አስተያየት አቀራረብ | 111 |

www.abyssinialaw.com



| | | |
|---|---|---|
| 30 | የተሻረ መመሪያ | 111 |
| 31 | መመሪያው ሥራ ላይ የሚውልበት ጊዜ | 111 |
| አባሪ አንድ | ነጻነትን እና ሕይወትን የሚያሳጡ የቅጣት እርከኖች ሠንጠረዥ | 112 |
| አባሪ ሁለት | የገንዘብ መቀጮ ሠንጠረዥ | 114 |

www.abyssinialaw.com

# መግቢያ

የወንጀል ሕግ ግብ ወንጀል እንዳይፈጸም መከላከል ሲሆን ይህንን ግብ የሚያሳካው በአንድ በኩል ስለ ወንጀሎችና ስለሚያስከትሉት ቅጣት በማሳወቅ ከወዲሁ ሰዎች ከወንጀል ሥራ እንዲቆጠቡ በማድረግ፣ ማስጠንቀቂያው በቂ ባልሆነ ጊዜ ጥፋት አድራጊዎች ተገቢውን ቅጣት እንዲያገኙ ማድረግ በመሆኑ፣

ቅጣት ወንጀልን የመከላከል ግቡን ሊያሳካ የሚችለው የሚጣለው ቅጣት ትክክለኛ፣ ወጥነት እና ተገማችነት ያለው ሲሆን፣ እንዲሁም ግልጽነትንና ተጠያቂነትን በሚያረጋግጥ መልኩ ተግባራዊ ሲደረግ በመሆኑ፣

በወንጀል ህጉ ጠቅላላ እና ልዩ ክፍል እንዲሁም በተለያዩ ሕጎች ስለ ቅጣት አወሳሰን ዝርዝር ድንጋጌዎች ቢኖሩም ብቻቸውን ትክክለኛነትን፣ ወጥነትን እና ተገማችነትን ለማረጋገጥ በቂ ባለመሆናቸው፣

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወንጀል ህጉ አንቀጽ 88(4) በተሰጠው ስልጣን መሠረት ከግንቦት 9 ቀን 2002 ጀምሮ ተግባራዊ የተደረገ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ አውጥቶ ሲተገበር የቆየ ሲሆን፣ በአተገባበር ያጋጠሙ ችግሮችን መሠረት በማድረግ መመሪያውን ማሻሻል በማስፈለጉ፣ እንዲሁም ደረጃ ባልወጣላቸው ተጨማሪ የወንጀል ህጉ ድንጋጌዎች ላይ የቅጣት መመሪያ እንዲወጣ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወንጀል ህግ አንቀጽ 88 ንኡስ አንቀጽ 4 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን የተሻሻለ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ አውጥቷል::

www.abyssinialaw.com

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ ድንጋጌዎች

## አንቀጽ 1. ስያሜ

ይህ መመሪያ የተሻሻለው የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 2. ትርጓሜ

1. ‹ፍርድ ቤት› ማለት የወንጀል ጉዳዮችን ለመዳኘት በህግ ሥልጣን የተሰጠው አካል ማለት ነው፡፡
2. ‹የወንጀል ደረጃ› ማለት በወንጀል አፈጻጸም ባህርያቸውና ከባድነታቸው አንጻር ለቅጣት አወሳሰን በተመሳሳይ ደረጃ ለማስቀመጥ እንዲቻል የወንጀል ድርጊት መመዘኛዎችን የያዘ ነው፡፡
3. ‹የቅጣት እርከን› ማለት የቅጣት መነሻና መድረሻ ያለው ቅጣቱ የሚወሰንበት እርከን ማለት ነው፡፡
4. ‹ፍቅድ ስልጣን› [range] ማለት ፍርድ ቤቶች የወንጀል አፈጻጸሙን ልዩ ሁኔታ ከግምት በማስገባት ቅጣቱን ለመጣል የሚችሉበት በቅጣት እርከን የተቀመጠው መነሻና መድረሻ ቅጣት መካከል ያለው የቅጣት መጠን ማለት ነው፡፡
5. ‹መነሻ ቅጣት› ማለት ቅጣቱን የሚያከብዱና የሚያቀሉ ጠቅላላ እና ልዩ ምክንያቶች ታሳቢ ከመደረጋቸው በፊት በፍርድ ቤቱ የቅጣት እርከኑን መሰረት በማድረግ የሚጣል ቅጣት ነው፡፡

## አንቀጽ 3. የመመሪያው ዓላማና ግብ

### 3.1. ዓላማ

የመመሪያው ዓላማ የዳኝነት አካሉ ግልጽነትና ተጠያቂነትን ባረጋገጠ መልኩ ውጤታማና ተገማችነት ያለው ቅጣት የሚሰጥበትን ሥርዓት መመስረት ነው፡፡

www.abyssinialaw.com

3.2. ግብ

መመሪያው የሚከተሉት ግቦች ይኖሩታል፡-

ሀ. በተቀራራቢና ተመሳሳይ የወንጀል ጉዳዮች መካከል ተቀራራቢነት ያለው ቅጣት እንዲወሰን ማድረግ፣

ለ. እንደ ወንጀሉ ክብደትና አደገኛነት የቅጣትን ተመጣጣኝነት ማረጋገጥ ነው፡፡

## አንቀጽ 4. መሠረታዊ ድንጋጌዎች

1. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 189 እንደተደነገገው ፍርድ ቤቶች ቅጣት ሲወስኑ ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶችን መሠረት አድርገው ቅጣቱን ከማክበዳቸው ወይም ከማቅለላቸው በፊት ከተጣሰው የወንጀል ድንጋጌ አንጻር የወንጀሉን ባህሪ መሠረት በማድረግ በቅድሚያ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 88(2) መሠረት መነሻ ቅጣቱን ይወስናሉ፡፡ በመቀጠልም ማክበጃ ምክንያቶችን መሰረት በማድረግ ቅጣቱን ያከብዳሉ፤ በመጨረሻም ማቅለያ ምክንያቶችን መሠረት በማድረግ ቅጣቱን ያቀላሉ፡፡
2. በቅጣት አወሳሰን ተመሳሳይና ተቀራራቢ የወንጀል ድርጊቶች መካከል ተመሳሳይና ተቀራራቢ ቅጣት ለመጣል ያስችል ዘንድ ድርጊቶቹን በተመሳሳይ የወንጀል ደረጃ የሚያስቀምጣቸውን መሠረታዊ ባህሪ መሠረት በማድረግ የቅጣት ውሳኔ ይሰጣል፡፡
3. በእያንዳንዱ የወንጀል ሕግ ድንጋጌ ወንጀሉን የሚያቋቁመው ፍሬነገር አንድና ተመሳሳይ ቢሆንም፣ ከአደገኛነታቸው ወይም ከሚያደርሱት ጉዳት አንጻር ልዩነት ሊደረግባቸው የሚገቡ የወንጀል ድርጊቶች እንደ ወንጀሉ ክብደትና አደገኛነት ደረጃ በማውጣት ቅጣት ይወሰናል፡፡
4. በወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል ለእያንዳንዱ የወንጀል ድርጊት የተደነገገው የቅጣት መነሻ ትርጉም እንዲኖረው ለማድረግ በአንቀጹ ከተቀመጠው መነሻ ቅጣት ጀምሮ እንደወንጀሉ ከባድነት መነሻው ከፍ እያለ በሚሄድ መልኩ ቅጣት ይወሰናል፡፡ ሆኖም ከአንዳንድ ወንጀሎች የተለየ ባህሪ የተነሣ ከመነሻው መጀመር ተመጣጣኝ እና ተገቢውን ቅጣት ለመወሰን የማያስችል ሆኖ ሲገኝ የወንጀል ህጉን አላማ ታሳቢ ባደረገ መልኩ መነሻ ቅጣቱ ከፍ ብሎ እንዲጀምር ይደረጋል፡፡

www.abyssinialaw.com

5. በወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል ለእያንዳንዱ የወንጀል ድርጊት የተደነገገው ጣሪያ ላይ የሚደረሰው ጠቅላላ ማክበጃ ምክንያቶች በሚኖሩበት ጊዜ መሆኑን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ከፍተኛው የወንጀል ደረጃ መነሻ ቅጣቱ ይወሰናል፡፡
6. የቅጣት ማክበጃዎችና ማቅለያዎች በተመሳሳይና ተቀራራቢ ደረጃ ለሚገኙ የወንጀል ድርጊቶች ወጥነት ባለው መልኩ ቅጣቱን የሚያከብዱ ወይም የሚያቀሉ ይሆናሉ፡፡ ሆኖም በወንጀል ሕጉ ስለ ልዩ የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶች የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ናቸው፡፡
7. ፍርድ ቤቶች መነሻ ቅጣቱን ለማስቀመጥ፣ እንዲሁም የቅጣት ማክበጃዎችና ማቅለያዎችን መሠረት በማድረግ ቅጣቱን ለማክበድ ወይም ለማቅለል ሲወስኑ እንደ ወንጀሉ ዓይነት ሊታዩ የሚገቡ ልዩ ሁኔታዎችን ታሳቢ በማድረግ በየቅጣት እርከኑ ባለው ፍቅድ ስልጣን ውስጥ አግባብነት ያለውን ቅጣት መወሰን ይችላሉ፡፡
8. በዚህ መመሪያ የወንጀል ደረጃ ያልወጣላቸው የወንጀል ድንጋጌዎችን በመጣስ የሚፈጸሙ የወንጀል ድርጊቶች ላይ የሚወሰነው ቅጣት በዚህ መመሪያ የወንጀል ደረጃ ለወጣላቸው የወንጀል ህጉ ድንጋጌዎች ላይ ቅጣት ለመጣል የተቀመጡትን አጠቃላይ ድንጋጌዎች፣ መስፈርቶችና አሰራሮችን እንደሁኔታው በመጠቀም ይሆናል፡፡
9. ይህ መመሪያ በወንጀል ሕግ ስለ ቅጣት አወሳሰን ከተቀመጡት ድንጋጌዎች ጋር በተጣጣመ መልኩ ይተረጎማል፡፡

www.abyssinialaw.com

# ክፍል ሁለት

## ነፃነትንና ሕይወትን የሚያሳጡ ቅጣቶችና የገንዘብ መቀጮ ሠንጠረዥ

### አንቀጽ 5. የቅጣት እርከኖች ሠንጠረዥ

በዚህ መመሪያ መሠረት የሚጣለው ቅጣት ለተመሳሳይና ተቀራራቢ የወንጀል ድርጊቶች ተመሳሳይ እና ተቀራራቢ ቅጣት ለመጣል እንዲቻል፣ እንዲሁም የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶች ቅጣቱን በተመሳሳይ መጠን እንዲያከብዱ ወይም እንዲያቀሉ ለማድረግ እንዲቻል ቅጣት የሚወሰነው ከዚህ መመሪያ ጋር በአባሪነት ተያይዞ በሚገኘው የቅጣት እርከን ሰንጠረዥ መሠረት ነው፡፡

### አንቀጽ 6. ነጻነትንና ሕይወትን የሚያሳጡ ቅጣቶች እርከን ሠንጠረዥ

1. ነጻነትንና ሕይወትን የሚያሳጡ ቅጣቶች እርከን ሠንጠረዥ ከቀላል እስራት እስከ ሞት ቅጣት ድረስ ያለውን ያካተተ ነው፡፡
2. ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም ሲባል በወንጀል ሕጉ በተመለከተው መሠረት ከዝቅተኛው ቅጣት (1 ቀን የግዴታ ሥራ) እስከ ከፍተኛው ቅጣት ሞት ድረስ የሚደርስ 39 የቅጣት እርከኖች ያሉት ሠንጠረዥ አባሪ አንድ ተዘጋጅቷል፡፡
3. ሠንጠረዡ ሲዘጋጅ ለእያንዳንዱ የቅጣት እርከን መነሻና መድረሻ ያለው ሲሆን፣ የሚከተሉትን መሠረተ ሀሳቦች መሠረት ባደረገ መልኩ የተዘጋጀ ነው፡፡
   ሀ. የቅጣት መነሻቸው ከእርከን 1 ጀምሮ እስከ ቅጣት እርከን 15 ድረስ በመነሻውና በመድረሻው መካከል የስድስት ወር ፍቅድ ሥልጣን (range) እንዲኖር ሆኖ ተዘጋጅቷል፡፡
   ለ. ከቅጣት እርከን 16 ጀምሮ በመነሻውና በመድረሻው መካከል ያለው ፍቅድ ስልጣን (range) የመነሻውን ሃያ በመቶ እንዲሆን ተደርጓል፡፡
   ሐ. በየደረጃው ያለው የቅጣት እርከን መነሻ ሲቀመጥ፣ ከቅጣት እርከኑ ዝቅ ብሎ ከነበረው የቅጣት እርከን መሀል/ በተለይም ከእርከን 16 ጀምሮ አማካይን

www.abyssinialaw.com

መነሻ በማድረግ የቅጣት መነሻና መድረሻው ተወስኗል፡፡ የቀድሞው እርከን አማካይ የቀጣዩ እርከን መነሻ ይሆናል፡፡

መ. በወንጀል ህጉ ቅጣቱ ከመነሻው እንደሚጀምር የተቀመጠ ስለሆነ፣ ለስሌቱ እንዲቀል የዝቅተኛው የቅጣት እርከን አማካዩ ብዙውን ጊዜ በወንጀሉ ከተቀመጡት መነሻዎች (1 አመት፣ 3 አመት፣ 5 አመት፣ 7 አመት፣ 10 አመት፣ 15 አመት) ጋር ያልተራራቀ በሆነ ጊዜ እነዚህ የቅጣት እርከኑ መነሻዎች እንዲሆኑ ተደርገዋል፡፡

ሠ. በወንጀል ህጉ ቁጥር 103(1) እስከ 6 ወር የሚደርስ ቀላል እስራት እስከ 6 ወር በሚደርስ የግዴታ ስራ ሊቀየር እንደሚችል ስለሚያስቀምጥ፣ ለዚህ መመሪያ አላማ የአንድ ቀን እስራት ከአንድ ቀን (8 ሰአት) የግዴታ ስራ ጋር ተመጣጣኝ ተደርጎ ተወስዷል፡፡ ስለሆነም የእስራት ቅጣቱ በማቅለያ ምክንያት የሚቀነስ ከሆነ ተቀንሶ በተደረሰበት የእስራት ቀናት ልክ የግዴታ ስራ እንዲሰራ ሊወሰን በሚችል መልኩ የቅጣት እርከኑ ተዘጋጅቷል፡፡

ረ. በቅጣት ማቅለያ ጊዜ የእስራት ቅጣት ወደ መቀጮ እንደሚቀየር የወንጀል ሕግ አንቀጽ 179 የሚደነግግ በመሆኑ ወደ መቀጮ ሲቀየር ስንት ሊሆን እንደሚችል በሚያሳይ መልኩም የቅጣት እርከኑ ተዘጋጅቷል፡፡

## አንቀጽ 7. የገንዘብ መቀጮ ሠንጠረዥ

1. በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 90(2) የተደነገጉትን መስፈርቶች መሠረት በማድረግ የወንጀሉን ክብደት ከግምት ባስገባ መልኩ የገንዘብ መቀጮ ጣሪያዎችን የሚያሳይ የቅጣት እርከን ሠንጠረዥ በአባሪ ሁለት ተዘጋጅቷል፡፡
2. በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 90(2) መሰረት የገንዘብ መቀጮን ለመወሰን የወንጀል አድራጊው የገቢ መጠን፣ ሀብቱ ወዘተ ከግምት ገብተው ስለሚወሠን በወንጀል ሕጉ ከተቀመጠው ጠቅላላ የመቀጮ ወለል ሌላ መነሻ የመቀጮ ቅጣት አልተቀመጠም፡፡
3. በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 92 በተደነገገው መሠረት ወንጀሉ በአፍቅሮ ንዋይ የተፈጸመ በሆነ ጊዜ ፍርድ ቤቶች በመቀጮ ቅጣት እርከን የተቀመጠውን ጣሪያ በአስር እጥፍ

www.abyssinialaw.com

በማሳደግ በወንጀል ሕጉ ከተመለከተው ጣሪያ ሳይበልጥ የመቀጮውን መጠን ሊወስኑ ይችላሉ፡፡

4. በልዩ ልዩ ሕጎች የተደነገገው የመቀጮ ጣሪያ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 90(1) ከተደነገገው በላይ ከሆነ፣ በልዩ ህጎች ላይ የተቀመጠውን ጣሪያ መሠረት በማድረግ መቀጮው ይሰላል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የወንጀል መነሻ ቅጣት ስለሚወሰንበት ሁኔታ

## ንዑስ ክፍል አንድ

## እንደ ወንጀሉ ክብደት ደረጃ የወጣላቸው የወንጀል ዓይነቶች ድንጋጌዎች እና የወንጀል ደረጃዎች

## ርዕስ አንድ

## በመንግስት ላይ የሚደረጉ ወንጀሎች

### አንቀጽ 8. የአገሪቱን የፖለቲካና የግዛት አንድነት በመንካት የሚደረግ ወንጀል (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 241)

1. በዚህ መመሪያ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 241 የአገሪቱን የፖለቲካና የግዛት አንድነት በመንካት በሚደረግ ወንጀል እና በወንጀል ሕግ አንቀጽ 257 በመገፋፋትና ግዙፍ ያልሆነ ማሰናዳት ተግባር ወንጀል ተከሰው ጥፋተኝነታቸው በፍርድ ቤት በሚረጋገጥባቸው ወንጀል አድራጊዎች ላይ ቅጣት የሚወሰነው ከዚህ ቀጥሎ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ነው፡፡
2. በወንጀል ህጉ አንቀጽ 241 ስር ቅጣትን ለመወሠን የወንጀሉን ማቋቋሚያ ነጥቦች፣ ጥፋተኛው የቡድን አባል መሆን አለመሆን፣ በወንጀሉ የደረሰውን ጉዳት፣ የጥፋተኛው ሥልጣን ደረጃ፣ እንዲሁም በወንጀሉ የተገኘ ጥቅም የሚሉ

www.abyssinialaw.com

መስፈርቶችን መሠረት በማድረግ ከዝቅተኛው እስከ ከፍተኛው አስር የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

3. ለዚህ መመሪያ ዓላማ ሲባል፣
   3.1 ቀላል ጉዳት ማለት በንብረት ላይ እስከ ብር 25,000 ጉዳት ያደረሰ ወይም በሰው ላይ ቀላል የአካል ጉዳት ያስከተለ እንደሆነ ነው
   3.2 መካከለኛ ጉዳት ማለት በንብረት ላይ ከብር 25,001 እስከ 50,000 ጉዳት ያደረሰ ወይም በሰው ላይ ከባድ የአካል ጉዳት ያስከተለ ነው፡፡
   3.3 ከባድ ጉዳት ማለት በንብረት ላይ ከብር 50,000 በላይ ጉዳት ያደረሰ ወይም ድርጊቱ ሞት ያስከተለ እንደሆነ ነው፡፡
4. የወንጀል ድርጊቱ በገንዘብ ወይም በንብረት ላይ ያስከተለው ጉዳት መጠን እና በሰው አካል ወይም ህይወት ላይ ያስከተለው የጉዳት መጠን የሚገኝበት ደረጃ የተለያየ በሚሆንበት ጊዜ ፍ/ቤቱ ቅጣቱን የሚወስነዉ ከሁለቱ ደረጃ የበለጠ ወይም ከፍ ያለ ቅጣት የሚያስከትለውን የጉዳት መጠን መሠረት በማድረግ ይሆናል፡፡
5. በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 241 ስር ጥፋተኛ የተባለ ተከሳሽ ከአስር አመት እስከ ሃያ አመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እስራት ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ በእድሜ ልክ ጽኑ እስራት ወይም በሞት ሊቀጣ እንደሚችል በድንጋጌው የተመለከተ ሲሆን፣ በተጨማሪነት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 259 መስፈርቶች ተሟልተው ሲገኙ እስከ ብር 100,000.00 (አንድ መቶ ሺህ) ሊደርስ የሚችል መቀጮ ሊያስከትል የሚችል ወንጀል በመሆኑ ከደረጃ ሰባት አንስቶ ላሉት የወንጀሉ ደረጃዎች ነጻነትን ከሚያሳጡ የቅጣቶች እርከን ጎን ለጎን የገንዘብ መቀጮ እርከኖች እንዲታከሉ ተደርጓል፡፡
6. ፍርድ ቤቱ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 241 ስር የሞት ቅጣትን በሚወስንበት ጊዜ ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 258 መስፈርቶች በተጨማሪ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 117 ድንጋጌዎችን ከግምት ማስገባት ይኖርበታል፡፡

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 9. መገፋፋትና ግዙፍ ያልሆነ የማሰናዳት ተግባር (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 257)

1. በዚህ መመሪያ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 257 በመገፋፋትና ግዙፍ ያልሆነ ማሰናዳት ተግባር ወንጀል ተከሰው ጥፋተኝነታቸው በፍርድ ቤት በሚረጋገጥባቸው ወንጀል አድራጊዎች ላይ ቅጣት የሚወሰነው ከዚህ ቀጥሎ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ነው፡፡
2. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 257 ስር በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ቅጣት ለመወሠን ከንዑስ ፊደል ‹‹ሀ›› እስከ ‹‹ሠ›› ስር ያሉት ድንጋጌዎች የያዟቸው የማቋቋሚያ ነጥቦች ክብደት፣ ወንጀሉ ሊያስከትል ይችል የነበረው አደጋ ከባድነት፣ የጥፋተኛው ሥልጣን ደረጃ፣ እንዲሁም በወንጀሉ የተገኘ ጥቅም የሚሉት መስፈርቶችን መሠረት በማድረግ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ስምንት የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡
3. ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 257 በወንጀል ድንጋጌው ስር ከንዑስ ፊደል ‹‹ሀ›› እስከ ‹‹ሠ›› በተዘረዘሩት ድንጋጌዎች እና በአንቀጽ 259 ላይ የተቀመጡ መስፈርቶችን መሠረት በማድረግ ስምንት ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡
4. የወንጀሉ ደረጃ 6 እና ደረጃ 8 ወንጀሉ ሊያስከትል ይችል የነበረውን አደጋ ከፍተኛነት መሠረት ያደረጉ ሲሆን በሁለቱም ደረጃዎች የአደጋውን ክብደት ፍርድ ቤቱ እንደነገሩ ሁኔታ እያየ ምክንያቱን በግልጽ በማስፈር ሊወስን ይችላል፡፡
5. ፍርድ ቤቱ ጥፋተኛው በደረጃ ሰባት የተመለከቱትን የሥልጣንና የጥቅም መስፈርቶች መሟላታቸውን እንደነገሩ ሁኔታ እያየ ምክንያቱን በግልጽ በማስፈር የሚወስን ይሆናል፡፡
6. በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 257 ስር ጥፋተኛ የተባለ ተከሳሽ በቀላል እስራት፤ ወይም ይህ አድራጎት ሊያስከትል ይችል የነበረው አደጋ በተለይ በጣም ከፍ ያለ እንደሆነ ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ሊቀጣ እንደሚችል በድንጋጌው የተመለከተ ሲሆን፣ በተጨማሪነት የአንቀጽ 259 መስፈርቶች ተሟልተው ሲገኙ እስከ ብር 100,000.00 (አንድ መቶ ሺህ) ሊደርስ የሚችል መቀጮ ሊያስከትል የሚችል ወንጀል በመሆኑ ከደረጃ 7 አንስቶ ላሉት የወንጀል ደረጃዎች ነጻነትን

www.abyssinialaw.com

ከሚያሳጡ የቅጣቶች እርከን ጎን ለጎን የገንዘብ መቀጮ እርከኖች እንዲታከሉ ተደርጓል፡፡

## የአገሪቱን የፖለቲካና የግዛት አንድነት በመንካት የሚደረግ ወንጀል

## (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 241)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| 241 | 1 | የተደራጀ የቡድን አባል ሳይሆን በድንጋጌው አግባብ ድርጊቱን የፈፀመና ጉዳቱ ቀላል ከሆነ | 29 | |
| 241 | 2 | የተደራጀ የቡድን አባል ሆኖ በድንጋጌው አግባብ ድርጊቱን የፈፀመና ጉዳቱ ቀላል ከሆነ | 30 | |
| 241 | 3 | የተደራጀ ቡድን አባል ሳይሆን በድንጋጌው አግባብ ድርጊቱ ከተፈፀመና ጉዳቱ መካከለኛ ከሆነ | 31 | |
| 241 | 4 | የተደራጀ ቡድን አባል ሆኖ ድርጊቱ በድንጋጌው አግባብ ከተፈፀመና የደረሰው ጉዳት መካከለኛ ከሆነ | 33 | |
| 241 | 5 | የተደራጀ ቡድን አባል ሣይሆን ድርጊቱ በድንጋጌው አግባብ ከተፈፀመና ጉዳቱ ከባድ ከሆነ | 34 | |

www.abyssinialaw.com

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 241 | 6 | የተደራጀ ቡድን አባል ሆኖ ድርጊቱ በድንጋጌው አግባብ በተፈፀመና ጉዳቱ ከባድ ከሆነ | 35 | |
| 241 እና 259 | 7 | በድንጋጌው የተመለከቱት ተግባራት የተፈፀሙት ተሿሚ ወይም መሪ በሆነ ሰው ወይም ጥቅም ለማግኘት ሆኖ ጉዳቱ ቀላል ከሆነ | 36 | 7 |
| 241 እና 259 | 8 | በድንጋጌው የተመለከቱት ተግባራት የተፈፀሙት ተሿሚ ወይም መሪ በሆነ ሰው ወይም ጥቅም ለማግኘት ሆኖ ጉዳቱ መካከለኛ ከሆነ | 37 | 10 |
| 241 እና 259 | 9 | በድንጋጌው የተመለከቱት ተግባራት የተፈፀሙት ተሿሚ ወይም መሪ በሆነ ሰው ሆኖ ጉዳቱ ከባድ ከሆነ | 38 | 11 |
| 241 እና 258 | 10 | በድንጋጌው ከተመለከቱት ተግባራት አንዱ ከተፈፀመና በአንቀፅ 258 ሥር ከተዘረዘሩት ፍሬ ነገሮች አንዱ ከተሟላ | 39 | 12 |

www.abyssinialaw.com

## መገፋፋትና ግዙፍ ያልሆነ የማሰናዳት ተግባር (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 257)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| 257 | 1 | አጥፊዉ ድርጊቱን በንግግር፣ በስዕል ወይም በጽሁፍ አማካይነት በግልጽ የቀሰቀሰ እንደሆነ | 2 | |
| 257 | 2 | አጥፊዉ ሽፍቶችን በአገር ዉስጥ ወይም ከአገር ዉጭም ቢሆን እንዲቋቋሙ ያደመ፣ ዕቅድ ያወጣ ወይም የገፋፋ እንደሆነ | 5 | |
| 257 | 3 | እንደዚህ በመሳሰሉ ሽፍቶች ቡድን የገባ፣ በእቅዱም የተባበረ ወይም ትዕዛዙን የተከተለ እንደሆነ | 8 | |
| 257 | 4 | ከዉጭ አገር መንግስታት፣ የፖለቲካ ወይም ሌላ ድርጅት ወይም ከእነዚሁ ወኪሎች ጋር ግንኙነት ያደረገ ወይም በምስጢር ግንኙነት የተባበረ እንደሆነ | 11 | |
| 257 | 5 | የህዝቡን ሞራል ዝቅ ለማድረግ እና እምነቱን ወይም የመቋቋም ኃይሉን ለማፍረስ በማቀድ በተቀናጀ ዘዴ ትክክለኛ ያልሆነ፣ ጥላቻ የተሞላበት ወይም ያለዉን አቋም የሚያፈርስ መረጃ በንግግር፣ በጽሁፍ ወይም በስዕል የበተነ ወይም ያስታወቀ | 14 | |

www.abyssinialaw.com

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | እንደሆነ | | |
| 257 | 6 | ከላይ ከተፈጸሙት ድርጊቶች መካከል አንዱ በጣም ከፍ ያለ አደጋ ሊያስከትል ይችል የነበረ እንደሆነ | 17 | |
| 257 እና 259 | 7 | በድንጋጌው የተመለከቱት ድርጊቶች የተፈጸሙት ተሿሚ ወይም መሪ በሆነ ሰው ወይም ጥቅም ለማግኘት ከሆነ | 20 | 8 |
| 257 እና 259 | 8 | በደረጃ 7 የተመለከቱት ፍሬ ነገሮች እንዳሉ ሆነው ድርጊቱ ከፍ ያለ አደጋ ሊያስከትል ይችል የነበረ ከሆነ | 23 | 11 |

## ርዕስ ሁለት

## በታወቁ ገንዘቦች፣ የግዴታ ወይም የዋስትና ሰነዶች፣ ማህተሞች፣ ቴምብሮች ወይም መሳሪያዎች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች

### አንቀጽ 10. የሐሰት ገንዘብ፣ የግዴታ ወይም የዋስትና ሰነዶች መስራት (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 356-362)

1. በዚህ መመሪያ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 356-362 የሐሰት ገንዘብ፣ የግዴታ ወይም የዋስትና ሰነዶች ጋር በተያያዘ በወንጀል ተከሰው ጥፋተኝነታቸው በፍርድ ቤት በሚረጋገጥባቸው ወንጀል አድራጊዎች ላይ ቅጣት የሚወሰነው ከዚህ ቀጥሎ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ነው፡፡
2. የወንጀል ሕግ አንቀጽ 362 ተግባራዊ የሚሆነው ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 356-361 የሚገኙትን ድንጋጌዎች በመተላለፍ የሚፈጸም ወንጀል የገንዘቡ ግምት አነስተኛ ግምት የሚሰጠው ሆኖ ወንጀሉ ቀላል በሚሆንበት ጊዜ በመሆኑ ለዚህ ርዕስ

www.abyssinialaw.com

አፈጻጸም እስከ ብር 1,000 /አንድ ሺህ ብር/ ግምት ያላቸው ወንጀሎች አነስተኛ ግምት ያላቸው ተደርገው ተወስደዋል፡፡

3. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 356-362 መሠረት ቅጣት ለመወሰን በወንጀሉ የተገኘው ወይም ሊገኝ የታሰበው የገንዘቡ ወይም ንብረቱ ጥቅም ግምትን መሠረት በማድረግ የጥቅሙን መጨመር ታሳቢ ባደረገ መልኩ እንዲሁም ወንጀሉ በቀላል ሁኔታ ከተደረገ ተፈጻሚነት ካለው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 362 ጋር መጣመር ለሚገባቸው ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ለእያንዳንዳቸው አምስት፣ ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 356 ዘጠኝ፣ ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 357 ዘጠኝ፣ ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 358 ዘጠኝ፣ ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 359 ዘጠኝ፣ ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 361/1/ሀ ዘጠኝ፣ ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 361/1/ለ ዘጠኝ፣ ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 361/2/ሀ አስራ አንድ እና ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 361/2/ለ አምስት የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 361/2/ሀ የሚደነግገው ቅጣት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 362 ስር እንደተመለከተው ቀላል እስራት በመሆኑ እና የወንጀል ሕግ አንቀጽ 361/2/ለ የሚደነግገው ቅጣት የገንዘብ መቀጮ በመሆኑ ሁለቱን ድንጋጌዎች ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 362 ጋር ማጣመር ሳያስፈልግ ራሳቸውን ችለው የወንጀል ደረጃዎች እንዲዘጋጅላቸው ተደርጓል፡፡

## መስራት (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 356 እና 362)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 356 እና 362 | 1 | እስከ ብር 100.00 | 2 |
| 356 እና 362 | 2 | ከብር 101.00-250.00 | 4 |

www.abyssinialaw.com

| | | | |
|---|---|---|---|
| 356 እና 362 | 3 | ከብር 251.00-500,00 | 6 |
| 356 እና 362 | 4 | ከብር 501.00-750.00 | 8 |
| 356 እና 362 | 5 | ከብር 751.00-1,000.00 | 10 |

## መስራት (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 356)

| | | | |
|---|---|---|---|
| 356 | 1 | ከብር 1,001.00-5,000.00 | 21 |
| 356 | 2 | ከብር 5,001.00-10,000.00 | 23 |
| 356 | 3 | ከብር 10,001.00-20,000.00 | 25 |
| 356 | 4 | ከብር 20,001.00-30,000.00 | 27 |
| 356 | 5 | ከብር 30,001.00-40,000.00 | 29 |
| 356 | 6 | ከብር 40,001.00-50,000.00 | 31 |
| 356 | 7 | ከብር 50,001.00-75,000.00 | 33 |
| 356 | 8 | ከብር 75,001.00-100,000 | 34 |
| 356 | 9 | ከብር 100,000 በላይ | 35 |

www.abyssinialaw.com

## ወደ ሐሰተኛነት መለወጥ (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 357 እና 362)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 357 እና 362 | 1 | እስከ ብር 100.00 | 2 |
| 357 እና 362 | 2 | ከብር 101.00-250.00 | 4 |
| 357 እና 362 | 3 | ከብር 251.00-500.00 | 6 |
| 357 እና 362 | 4 | ከብር 501.00-750.00 | 8 |
| 357 እና 362 | 5 | ከብር 751.00-1,000.00 | 10 |

## ወደ ሐሰተኛነት መለወጥ (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 357)

| | | | |
|---|---|---|---|
| 357 | 1 | ከብር 1,001.00-5,000.00 | 7 |
| 357 | 2 | ከብር 5,001.00-10,000.00 | 10 |
| 357 | 3 | ከብር 10,001.00-20,000.00 | 13 |
| 357 | 4 | ከብር 20,001.00-30,000.00 | 16 |

www.abyssinialaw.com

| | | | |
|---|---|---|---|
| 357 | 5 | ከብር 30,001.00-40,000.00 | 19 |
| 357 | 6 | ከብር 40,001.00-50,000.00 | 22 |
| 357 | 7 | ከብር 50,001.00-75,000.00 | 25 |
| 357 | 8 | ከብር 75,001.001-100,000 | 28 |
| 357 | 9 | ከብር 100,000 በላይ | 31 |

## ዋጋውን ዝቅ ማድረግ (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 358 እና 362)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 358 እና 362 | 1 | እስከ ብር 100.00 | 2 |
| 358 እና 362 | 2 | ከብር 101.00-250.00 | 4 |
| 358 እና 362 | 3 | ከብር 251.00-500.00 | 6 |
| 358 እና 362 | 4 | ከብር 501.00-750.00 | 8 |
| 358 እና 362 | 5 | ከብር 751.00-1,000.00 | 10 |

www.abyssinialaw.com

## ዋጋውን ዝቅ ማድረግ (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 358)

| | | | |
|---|---|---|---|
| 358 | 1 | ከብር 1,001.00-5,000.00 | 7 |
| 358 | 2 | ከብር 5,001.00-10,000.00 | 9 |
| 358 | 3 | ከብር 10,001.00-20,000.00 | 11 |
| 358 | 4 | ከብር 20,001.00-30,000.00 | 13 |
| 358 | 5 | ከብር 30,001.00-40,000.00 | 15 |
| 358 | 6 | ከብር 40,001.00-50,000.00 | 17 |
| 358 | 7 | ከብር 50,001.00-75,000.00 | 19 |
| 358 | 8 | ከብር 75,000.00-100,000 | 21 |
| 358 | 9 | ከብር 100,000 በላይ | 23 |

## ወደ አገር ማስገባት፣ ከአገር ማስወጣት፣ መያዝ፣ ማስቀመጥ እና ማቅረብ (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 359 እና 362)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 359 እና 362 | 1 | እስከ ብር 100.00 | 2 |

www.abyssinialaw.com

| | | | |
|---|---|---|---|
| 359 እና 362 | 2 | ከብር 101.00-250.00 | 4 |
| 359 እና 362 | 3 | ከብር 251.00-500.00 | 6 |
| 359 እና 362 | 4 | ከብር 501.00-750.00 | 8 |
| 359 እና 362 | 5 | ከብር 751.00-1,000.00 | 10 |

## ወደ አገር ማስገባት፣ ከአገር ማስወጣት፣ መያዝ፣ ማስቀመጥ እና ማቅረብ (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 359)

| | | | |
|---|---|---|---|
| 359 | 1 | ከብር 1,001.00-5,000.00 | 7 |
| 359 | 2 | ከብር 5,001.00-10,000.00 | 10 |
| 359 | 3 | ከብር 10,001.00-20,000.00 | 13 |
| 359 | 4 | ከብር 20,001.00-30,000.00 | 16 |
| 359 | 5 | ከብር 30,001.00-40,000.00 | 19 |
| 359 | 6 | ከብር 40,001.00-50,000.00 | 22 |
| 359 | 7 | ከብር 50,001.00-75,000.00 | 25 |

www.abyssinialaw.com

| | | | |
|---|---|---|---|
| 359 | 8 | ከብር 75,000.00-100,000 | 28 |
| 359 | 9 | ከብር 100,000 በላይ | 31 |

## ማዘዋወር (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 361/1/ሀ እና 362)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 361/1/ሀ እና 362 | 1 | እስከ ብር 100.00 | 2 |
| 361/1/ሀ እና 362 | 2 | ከብር 101.00-250.00 | 4 |
| 361/1/ሀ እና 362 | 3 | ከብር 251.00-500.00 | 6 |
| 361/1/ሀ እና 362 | 4 | ከብር 501.00-750.00 | 8 |
| 361/1/ሀ እና 362 | 5 | ከብር 751.00-1,000.00 | 10 |

www.abyssinialaw.com

## ማዘዋወር (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 361/1/ሀ)

| | | | |
|---|---|---|---|
| 361/1/ሀ | 1 | ከብር 1,001.00-5,000.00 | 7 |
| 361/1/ሀ | 2 | ከብር 5,001.00-10,000.00 | 9 |
| 361/1/ሀ | 3 | ከብር 10,001.00-20,000.00 | 11 |
| 361/1/ሀ | 4 | ከብር 20,001.00-30,000.00 | 13 |
| 361/1/ሀ | 5 | ከብር 30,001.00-40,000.00 | 15 |
| 361/1/ሀ | 6 | ከብር 40,001.00-50,000.00 | 17 |
| 361/1/ሀ | 7 | ከብር 50,001.00-75,000.00 | 19 |
| 361/1/ሀ | 8 | ከብር 75,000.00-100,000 | 21 |
| 361/1/ሀ | 9 | ከብር 100,000 በላይ | 23 |

## ማዘዋወር (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 361/1/ለ እና 362)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| 361/1/ለ እና 362 | 1 | እስከ ብር 100.00 | 2 | 1 |
| 361/1/ለ እና 362 | 2 | ከብር 101.00-250.00 | 4 | 1 |

www.abyssinialaw.com

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 361/1/ለ እና 362 | 3 | ከብር 251.00-500.00 | 6 | 1 |
| 361/1/ለ እና 362 | 4 | ከብር 501.00-750.00 | 8 | 2 |
| 361/1/ለ እና 362 | 5 | ከብር 751.00-1,000.00 | 10 | 2 |

## ማዘዋወር (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 361/1/ለ)

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 361/1/ለ | 1 | ከብር 1,001.00-5,000.00 | 4 | 3 |
| 361/1/ለ | 2 | ከብር 5,001.00-10,000.00 | 6 | 3 |
| 361/1/ለ | 3 | ከብር 10,001.00-20,000.00 | 8 | 4 |
| 361/1/ለ | 4 | ከብር 20,001.00-30,000.00 | 10 | 4 |
| 361/1/ለ | 5 | ከብር 30,001.00-40,000.00 | 12 | 5 |
| 361/1/ለ | 6 | ከብር 40,001.00-50,000.00 | 14 | 5 |
| 361/1/ለ | 7 | ከብር 50,001.00-75,000.00 | 16 | 6 |
| 361/1/ለ | 8 | ከብር 75,000.00-100,000 | 18 | 6 |
| 361/1/ለ | 9 | ከብር 100,000 በላይ | 20 | 6 |

www.abyssinialaw.com

## ማዘዋወር (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 361/2/ሀ)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 361/2/ሀ | 1 | እስከ ብር 100.00 | 2 |
| 361/2/ሀ | 2 | ከብር 101.00-250.00 | 3 |
| 361/2/ሀ | 3 | ከብር 251.00-500.00 | 4 |
| 361/2/ሀ | 4 | ከብር 501.00-750.00 | 5 |
| 361/2/ሀ | 5 | ከብር 751.00-1,000.00 | 6 |
| 361/2/ሀ | 6 | ከብር 1,001.00-10,000.00 | 7 |
| 361/2/ሀ | 7 | ከብር 10,001.00-25,000.00 | 8 |
| 361/2/ሀ | 8 | ከብር 25,001.00-50,000.00 | 9 |
| 361/2/ሀ | 9 | ከብር 50,001.00-75,000.00 | 10 |
| 361/2/ሀ | 10 | ከብር 75,001.00-100,000.00 | 11 |
| 361/2/ሀ | 11 | ከብር 100,000.00 በላይ | 12 |

www.abyssinialaw.com

## ማዘዋወር (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 361/2/ለ)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 361/2/ለ | 1 | እስከ ብር 100.00 | 1 |
| 361/2/ለ | 2 | ከብር 101.00-1,000.00 | 1 |
| 361/2/ለ | 3 | ከብር 1,001.00-10,000.00 | 2 |
| 361/2/ለ | 4 | ከብር 10,001.00-50,000.00 | 3 |
| 361/2/ለ | 5 | ከብር 50,001.00-75,000.00 | 4 |
| 361/2/ለ | 6 | ከብር 75,000.00-100,000.00 | 5 |
| 361/2/ለ | 6 | ከብር 100,000.00 በላይ | 6 |

www.abyssinialaw.com

## ርዕስ ሦስት

## በመንግስት ሥራ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች

### አንቀጽ 11. በሥልጣን ያለአግባብ መገልገል (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 407)

1. በዚህ መመሪያ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 407 በሥልጣን ያለአግባብ መገልገል ወንጀል ተከሰው ጥፋተኝነታቸው በፍርድ ቤት በሚረጋገጥባቸው ወንጀል አድራጊዎች ላይ ቅጣት የሚወሰነው ከዚህ ቀጥሎ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ነው፡፡
2. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 407 መሠረት ቅጣትን ለመወሰን በድንጋጌው ንዑስ አንቀጽ 2 ውስጥ ያሉት መስፈርቶችን ማለትም የስልጣን ደረጃው፣ በወንጀሉ የተገኘው ወይም ሊገኝ የታሰበው ጥቅም ወይም የደረሰ ወይም ሊደርስ የታሰበው ጉዳት እና ወንጀሉ የተፈጸመበትን ዓላማ መሠረት በማድረግ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ፣ ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 407/1 አምስት፣ ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 407/2 አራት እና ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 407/3 ሦስት የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡
3. ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም፡-
   ሀ. ‹ከፍተኛ ሥልጣን› ማለት በተሻሻለው የፌዴራል ሥነምግባርና ጸረ ሙስና ኮሚሽን አዋጅ ቁጥር 433/97 አንቀጽ 2/5 ውስጥ የተካተቱት ባለስልጣኖች ያላቸው ሥልጣን ማለት ነው፡፡
   ለ. ‹መካከለኛ ስልጣን› ማለት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ‹ሀ› ውስጥ የማይካተቱ ነገር ግን ውሳኔ የሚወስኑ የሥራ ኃላፊነት ቦታዎች ማለትም የመምሪያ ኀላፊዎች፣ የሥራ ሂደት መሪዎች፣ ለመስሪያ ቤቱ የበላይ ኀላፊ ተጠሪ የሆኑ ኀላፊዎች፣ የዞን ኀላፊዎች፣ የወረዳ ኀላፊዎችና በዞንና በወረዳ መስተዳድሮች መምሪያ ኀላፊዎችንና ከእነዚህ ጋር ተመሳሳይ ስልጣን ያላቸውን ያካትታል፡፡
   ሐ. ‹ዝቅተኛ ሥልጣን› ማለት መካከለኛ የስልጣን ሀላፊነት በሚለው ውስጥ የማይካተቱ ዝቅተኛ ስራ መደብ ላይ የሚገኙ የመንግስት ሠራተኞችን ሥልጣን ማለት ነው፡፡
   መ. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 3 ከፊደል ሀ-ሐ የተመለከቱት የሥልጣን ደረጃ ትርጓሜዎች እንደተጠበቁ ሆኖ በክልል የስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች

www.abyssinialaw.com

ማቋቋሚያ አዋጆች ወይም አግባብነት ያላቸው ሌሎች ሕጎች ውስጥ የተመለከቱ ትርጓሜዎች ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

4. ጥቅም/ጉዳት ማለት የተገኘን ወይም ሊገኝ የታሰበውን ጥቅም እንዲሁም የደረሰውን ወይም ሊደርስ የታሰበውን ጉዳት የሚያካትት ሆኖ ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም፡-
   ሀ. ‹በጣም ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት› ማለት በወንጀል ድርጊቱ የተገኘው ጥቅም ወይም የደረሰው ጉዳት ከብር 500,000.00 (አምስት መቶ ሺህ) በላይ ሲሆን ነው፡፡
   ለ. ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት ማለት በወንጀል ድርጊቱ የተገኘው ጥቅም ወይም የደረሰው ጉዳት ከብር 100,001.00 (አንድ መቶ ሺህ አንድ) እስከ ብር 500,000.00 (አምስት መቶ ሺህ) ሲሆን ነው፡፡
   ሐ. ‹መካከለኛ ጥቅም/ጉዳት› ማለት በወንጀል ድርጊቱ የተገኘው ጥቅም ወይም የደረሰው ጉዳት ከብር 25,001.00 (ሃያ አምስት ሺህ አንድ) እስከ ብር 100,000.00 (አንድ መቶ ሺህ) ሲሆን ነው፡፡
   መ. ‹ዝቅተኛ ጥቅም/ጉዳት› ማለት በወንጀል ድርጊቱ የተገኘው ጥቅም ወይም የደረሰው ጉዳት ከብር 1,001.00 (አንድ ሺህ አንድ) እስከ ብር 25,000.00 (ሃያ አምስት ሺህ) ሲሆን ነው፡፡
   ሠ. ‹በጣም ዝቅተኛ ጥቅም/ጉዳት› ማለት በወንጀል ድርጊቱ የተገኘው ጥቅም ወይም የደረሰው ጉዳት እስከ ብር 1,000.00 (አንድ ሺህ) ሲሆን ነው፡፡

5. ከባድ ዓላማ፡- ማለት ጥቅም ወይም መብት ላይ የደረሰ ጉዳትን ለመመዘን ከተሰጠው ትርጉም ውጪ በተሻሻለው የፌዴራል ሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 433/97 አንቀፅ 2/9/ሀ/ሐ ስር በተሰጠው ትርጓሜ መሠረት የተፈፀመ ወንጀል ሲሆን ነው፡፡

6. በተፈጸመው ወንጀል የተገኘው የገንዘብ ጥቅም ወይም የደረሰውን ጉዳት በገንዘብ ገምቶ ለማስቀመጥ የማይቻል በሆነ ጊዜ ፍ/ቤቱ እንደነገሩ ሁኔታ ምክንያቱን በማስቀመጥ የተገኘውን የገንዘብ ጥቅም ወይም የደረሰውን የጉዳት መጠን ደረጃ ይወስናል፡፡

7. በተፈጸመው ወንጀል የተገኘው ጥቅም እና የደረሰው ጉዳት የሚታወቅ ከሆነ ደረጃውን ለመወሰን ከሁለቱ የሚበልጠው ይወሰዳል፡፡

www.abyssinialaw.com

8. የመንግሥት ሠራተኛ ያልሆነ ሰው በወ/ህ/አ.33 መሠረት ጥፋተኛ መሆኑ ከተረጋገጠ የወንጀል ደረጃ እና የቅጣት እርከኑ የሚወሰነው የመንግሥት ሠራተኛ የሆነው ሰው የወንጀል ደረጃ እና የቅጣት እርከን በተወሠነበት አግባብ ነው፡፡

## በሥልጣን ያለአግባብ መገልገል (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 407/1)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| 407/1 | 1 | ዝቅተኛ ሥልጣን እና በጣም ዝቅተኛ ጥቅም/ጉዳት | 7 | 2 |
| 407/1 | 2 | ዝቅተኛ ሥልጣን እና ዝቅተኛ ጥቅም/ጉዳት | 11 | 3 |
| 407/1 | 3 | ዝቅተኛ ሥልጣን እና መካከለኛ ጥቅም/ጉዳት | 15 | 4 |
| 407/1 | 4 | መካከለኛ ሥልጣን እና ዝቅተኛ ጥቅም/ጉዳት | 19 | 5 |
| 407/1 | 5 | መካከለኛ ሥልጣን እና መካከለኛ ጥቅም/ጉዳት | 23 | 6 |

www.abyssinialaw.com

## በሥልጣን ያለአግባብ መገልገል (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 407/2)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| 407/2 | 1 | ከፍተኛ ስልጣን እና በጣም ዝቅተኛ ጥቅም/ጉዳት/ ወይም ከባድ ዓላማና በጣም ዝቅተኛ ጥቅም/ጉዳት/ | 25 | 7 |
| 407/2 | 2 | ከፍተኛ ስልጣን እና ዝቅተኛ ጥቅም/ጉዳት ወይም፣ ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት እና ዝቅተኛ ስልጣን ወይም ከባድ ዓላማ እና ዝቅተኛ ስልጣን ወይም ከባድ ዓላማ እና ጥቅም/ጉዳት | 26 | 8 |
| 407/2 | 3 | ከፍተኛ ስልጣንና መካከለኛ ጥቅም/ጉዳት ወይም ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት እና መካከለኛ ስልጣን ወይም ከባድ ዓላማና መካከለኛ ጥቅም/ጉዳት ወይም ከባድ ዓላማና መካከለኛ ስልጣን | 27 | 9 |
| 407/2 | 4 | በጣም ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት እና መካከለኛ ስልጣን | 28 | 10 |

www.abyssinialaw.com

## በሥልጣን ያለአግባብ መገልገል (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 407/3)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| 407/3 | 1 | ከፍተኛ ስልጣን እና ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት፣ ወይም ከፍተኛ ስልጣንና ከባድ ዓላማ፤ ወይም ከባድ ዓላማና ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት | 29 | 10 |
| 407/3 | 2 | ከፍተኛ ስልጣን፣ ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት እና ከባድ ዓላማ ወይም ከፍተኛ ስልጣን እና በጣም ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት ወይም ከባድ ዓላማና በጣም ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት | 32 | 11 |
| 407/3 | 3 | ከፍተኛሥልጣን፣በጣም ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት እና ከባድ ዓላማ | 35 | 12 |

www.abyssinialaw.com

# ርዕስ አራት

# በሰው ሕይወት፣ አካልና ጤንነት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች

## ምዕራፍ አንድ

## በሰው ሕይወት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች

### አንቀጽ 12. በሰው ሕይወት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 539-543)

1. በዚህ መመሪያ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 539-543 ተከሰው ጥፋተኝነታቸው በፍርድ ቤት በሚረጋገጥባቸው ወንጀል አድራጊዎች ላይ ቅጣት የሚወሰነው ከዚህ ቀጥሎ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ነው፡፡
2. በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 539 ስር በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ቅጣትን ለመወሰን በእያንዳንዱ ድንጋጌ ሥር ያሉትን የወንጀሉን ማቋቋሚያ ነጥቦች፣ የነጥቦቹን ተደራርቦ መገኘትና የወንጀሉ ድርጊት አፈፃፀም ከባድ ወይም እጅግ በጣም ከባድ መሆኑን መሠረት በማድረግ ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡ በዚሁ መሠረት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 539/1 ከፊደል "ሀ" እስከ "ሐ" ለተመለከቱት ንዑስ ድንጋጌዎች ለእያንዳንዳቸው ሁለት ደረጃዎች የተዘጋጁ ሲሆን ለአንቀፅ ንዑስ ቁጥር ሁለት ደግሞ ቅጣቱ አማራጭ የሌለው በመሆኑ አንድ ደረጃ ብቻ እንዲኖረው ተደርጓል፡፡
3. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 539/1/ለ/ሐ ስር ለተመለከቱት ድንጋጌዎች ደረጃዎችን ለመለየት ፍርድ ቤቱ አስቀድሞ የወንጀሉ አፈፃፀም እጅግ ከባድ መሆን ያለመሆኑን ሊወስን ይገባል፡፡
4. የወንጀል አፈፃፀሙ እጅግ ከባድ ወይም ከዚያ በመለስ ያለነው ብሎ ለመለየትና ቅጣቱን ለመወሰን ከድንጋጌው በተጨማሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 117/1 መስፈርቶችን ታሳቢ በማድረግ መሆን ይኖርበታል፡፡
5. ለወንጀል ህግ አንቀጽ 540 ድንጋጌ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 539 የተመለከተውን ያህል ከባድ እንዲሁም በአንቀጽ 541 የተመለከተውን ያህል ቀላል አለመሆኑን

www.abyssinialaw.com

በመግለጽ ሕግ አውጭው ያስቀመጠውን ቅጣት መሠረት በማድረግ ስድስት ደረጃዎች እንዲኖሩት ተደርጓል፡፡

6. ለወንጀል ህግ አንቀጽ 540 ደረጃዎችን ለማውጣት ያገለገሉ መስፈርቶች የፀቡ ምክንያት፣ መሣሪያ አጠቃቀም ወይም ዘዴ እና የአገዳደሉ ሁኔታ የሚሉት ናቸው፡፡ ሆኖም በወንጀል ህግ አንቀጽ 540 ሥር የሚወድቀው ድርጊት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 539 እና በወንጀል ህግ አንቀጽ 541 ከሚሸፈኑ ድርጊቶች ውጭ በመሆኑ በወንጀል ህግ አንቀጽ 82/1/መ ሥር ያለው የተበዳይ ለድርጊቱ መንስኤ መሆን በጠቅላላ ቅጣት ማቅለያነት የሚያዝ አይሆንም፡፡
7. ለወንጀል ህግ አንቀጽ 540፣ 541/ለ/ እና 543 የወንጀል ደረጃን ለመወሠን የመሣሪያውን አደገኛ መሆን እና አለመሆን ፍ/ቤቱ አስቀድሞ ሊወስን ይገባል፡፡
8. ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 541 በድንጋጌው ንዑስ "ሀ" ሥር የተመለከተው ቅጣት በሚያጋጥም ጊዜ ፍርድ ቤት በመሰለው ቅጣትን ሊያቀል እንደሚችል ሕግ አውጭው የደነገገ በመሆኑ ደረጃ አልተዘጋጀለትም፡፡
9. ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 541 በድንጋጌው "ለ" ሥር ያሉትን ፍሬ ነገሮች መሠረት በማድረግ ሦስት ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡ ሆኖም ደረጃዎቹን ለማዘጋጀት ጥቅም ላይ የዋሉ ፍሬ ነገሮች በድጋሚ ማቅለያ ሆነው ቅጣትን እንዳያቀሉ ፍ/ቤቱ ተገቢው ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል፡፡
10. ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 543 በድንጋጌው ውስጥ የተመለከቱትን ፍሬ ነገሮች መሠረት በማድረግ ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 543/1 ስድስት፣ ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 543/2 አራት እና ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 543/3 ሦስት ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡
11. ፍርድ ቤት በወ/ህ/አ. 543 መሠረት የጥፋተኝነት ውሣኔ ሲሰጥ እንደ ድርጊቱ አፈፃፀም በወንጀል ህግ አንቀጽ 59 ሥር የተቀመጡትን መስፈርቶች በመጠቀም ቸልተኝነቱ የታወቀ (የወ/ህ/አ.59/1/ሀ) ወይም ያልታወቀ (የወ/ህ/አ.59/1/ለ) መሆኑን መወሰን አለበት፡፡

www.abyssinialaw.com

## ከባድ የሰው ግድያ (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 539/1/ሀ)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 539/1/ሀ | 1 | አስቀድሞ በማሰብ የተፈፀመ ሆኖ አፈፃፀሙ ከባድ ከሆነ ወይም በአፈጻጸሙ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 84/1 ስር የተመለከቱት ፊደሎች ካስቀመጧቸው የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች መካከል ሁለት እና ከዚያ በታች የሆኑ ምክንያቶች የተገኙ ከሆነ ወይም በወንጀል ሕግ አንቀጽ 86 መሠረት ሊያዝ የሚገባ ሁለት ወይም ከዚያ በታች የሆነ ሌላ ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት የተገኘ ከሆነ | 38 |
| 539/1/ሀ | 2 | አስቀድሞ በማሰብ የተፈጸመ ሆኖ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 84 ወይም 86 መሠረት ሊያዙ የሚችሉ ከሁለት በላይ ቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች ከተገኙ ወይም የወንጀሉ አፈጻጸም እጅግ በጣም ከባድ ከሆነ | 39 |

www.abyssinialaw.com

## ከባድ የሰው ግድያ (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 539/1/ለ)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 539/1/ለ | 1 | ሰውን ለመግደል ወይም የውንብድና ወንጀልን ለመፈጸም የተደራጀ ወንበዴ ቡድን አባል በመሆን ድርጊቱን መፈፀምና የድርጊቱ አፈጻፀም ከባድ ሆኖ መገኘት | 38 |
| 539/1/ለ | 2 | ሰውን ለመግደል ወይም የውንብድና ወንጀልን ለመፈጸም የተደራጀ ወንበዴ ቡድን አባል በመሆን ድርጊቱን መፈፀምና የድርጊቱ አፈጻጸም እጅግ በጣም ከባድ ሆኖ መገኘት | 39 |

## ከባድ የሰው ግድያ (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 539/1/ሐ)

| የወንጀ ል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 5391/ሐ | 1 | ሌላ ወንጀል ለመፈፀም እንዲመቸው ወይም የተፈጸመ ወንጀል እንዳይገለፅ ለማድረግ የተፈጸመ መሆኑና አፈጻጸሙ ከባድ ሆኖ መገኘት | 38 |
| 539/1/ ሐ | 2 | ሌላ ወንጀል ለመፈፀም እንዲመቸው ወይም የተፈጸመ ወንጀል እንዳይገለፅ ለማድረግ የተፈጸመ መሆኑና አፈጻጸሙ እጅግ በጣም ከባድ ሁኖ መገኘት | 39 |

www.abyssinialaw.com

## ከባድ የሰው ግድያ (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 539/2)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 539/2 | 1 | ወንጀለኛው የእድሜ ልክ ጽኑ እስራት ተፈርዶበት ቅጣቱን በመፈጸም ላይ ሳለ በአንቀፅ 539(1) በተመለከተው ሁኔታ ድርጊቱን ከፈጸመ | 39 |

## ተራ የሆነ የሰው ግድያ (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 540)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 540 | 1 | ለወንጀል ድርጊቱ መፈፀም መንስኤው ሟች ከሆነና አጥፊው ምንም ዓይነት መሣሪያ (ዘዴ) ካልተጠቀመ | 21 |
| 540 | 2 | በደረጃ 1 የተመለከተው የአጥፊው መመዘኛ እንዳለ ሆኖ አደገኛ ያልሆኑ መሣሪያዎችን (ዘዴ) ከተጠቀመ | 23 |
| 540 | 3 | በደረጃ 1 የተመለከተው መመዘኛ እንዳለ ሆኖ አጥፊው አደገኛ ሊባሉ የሚችሉ እንደ ጦር መሳሪያ፣ ስለት የመሳሰሉትን መሣሪያዎች (ዘዴ) ከተጠቀመ | 25 |
| 540 | 4 | ለወንጀል ድርጊቱ መንስኤ አጥፊው ከሆነና ምንም ዓይነት መሣሪያ(ዘዴ) ካልተጠቀመ | 27 |

www.abyssinialaw.com

| | | | |
|---|---|---|---|
| 540 | 5 | በደረጃ 4 የተመለከተው መመዘኛ እንዳለ ሆኖ አደገኛ ያልሆነ መሣሪዎችን (ዘዴ) ከተጠቀመ | 30 |
| 540 | 6 | በደረጃ 4 የተመለከተው መመዘኛ እንዳለ ሆኖ አደገኛ ሊባሉ የሚችሉ እንደ ጦር መሣሪያ (ዘዴ) ስለት ነገሮች የመሣሰሉትን ከተጠቀመ | 33 |

## ቀላል የሆነ የሰው ግድያ (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 541/ለ)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 541/ለ | 1 | በድንጋጌው ስር በተመለከተው አግባብ ድርጊቱን የፈፀመው ያለምንም መሣሪያ (ዘዴ) ከሆነ | 4 |
| 541/ለ | 2 | በደረጃ 1 የተመለከተው መመዘኛ እንዳለ ሆኖ ድርጊቱን የፈፀመው አደገኛ ሊባሉ በማይችሉ መሣሪያዎች (ዘዴ) ከሆነ፤ | 10 |
| 541/ለ | 3 | በደረጃ 1 የተመለከተው መመዘኛ እንዳለ ሆኖ ድርጊቱ የተፈፀመው አደገኛ ሊባሉ በሚችሉ እንደ ጦር መሣሪያ፣ (ዘዴ) ስለት የመሣሣሉት ነገሮች ከሆነ | 16 |

www.abyssinialaw.com

# በቸልተኝነት ሰውን መግደል (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 543/1)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| 543/1 | 1 | የወንጀል ድርጊቱ የተፈፀመው ያለምንም መሣሪያ እና ባልታወቀ ቸልተኝነት ከሆነ | 5 | 2 |
| 543/1 | 2 | የወንጀል ድርጊቱ የተፈፀመው ያለምንም መሣሪያ እና በታወቀ ቸልተኝነት ከሆነ | 6 | 2 |
| 543/1 | 3 | የወንጀል ድርጊቱ የተፈፀመው አደገኛ ባልሆነ መሣሪያ እና ባልታወቀ ቸልተኝነት ከሆነ | 7 | 4 |
| 543/1 | 4 | የወንጀል ድርጊቱ የተፈፀመው አደገኛ ባልሆነ መሣሪያ እና በታወቀ ቸልተኝነት ከሆነ | 8 | 3 |
| 543/1 | 5 | ድርጊቱ የተፈፀመው በአደገኛ መሣሪያ እና ባልታወቀ ቸልተኝነት ከሆነ | 9 | 4 |
| 543/1 | 6 | ድርጊቱ የተፈፀመው በአደገኛ መሣሪያ እና በታወቀ ቸልተኝነት ከሆነ | 10 | 4 |

www.abyssinialaw.com

## በቸልተኝነት ሰውን መግደል (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 543/2)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| 543/2 | 1 | አጥፊው የሙያ ወይም ሌላ ግዴታ ያለው ሆኖ ድርጊቱም የሚች አስተዋፅኦ ካለው እና ባልታወቀ ቸልተኝነት የተፈፀመ ከሆነ | 7 | 3 |
| 543/2 | 2 | አጥፊው የሙያ ወይም ሌላ ግዴታ ያለው ሆኖ ድርጊቱም የሚች አስተዋፅኦ ከሌለበት እና ባልታወቀ ቸልተኝነት፣ ድርጊቱን ከፈፀመ፣ | 8 | 4 |
| 543/2 | 3 | አጥፊው የሙያ ወይም ሌላግዴታ ያለው ሆኖ ድርጊቱም የሚች አስተዋፅኦ ካለበት እና በታወቀ ቸልተኝነት ድርጊቱ ከተፈፀመ፣ | 14 | 4 |
| 543/2 | 4 | የሙያ ወይም ሌላ ግዴታ ያለበት ሆኖ ድርጊቱም የሚች አሰተዋፅኦ ከሌለበት እና ድርጊቱ በታወቀ ቸልተኝነት ከተፈፀመ | 16 | 4 |

www.abyssinialaw.com

## በቸልተኝነት ሰውን መግደል (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 543/3)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| 543/3 | 1 | በድንጋጌው ከተመለከቱት ውስጥ አንዱ ፍሬነገር (ማቋቋሚያ)ከተሟላ | 21 | 6 |
| 543/3 | 2 | በድንጋጌው ከተመለከቱት ውስጥ ሁለት ፍሬ ነገሮች (ማቋቋሚያዎች) ከተሟሉ | 25 | 7 |
| 543/3 | 3 | በድንጋጌው ከተመለከቱት ፍሬ ነገሮች (ማቋቋሚያዎች) ውስጥ ሶስት እና ከዛ በላይ ከተሟሉ | 29 | 7 |

www.abyssinialaw.com

# ምዕራፍ ሁለት

# በሰው አካልና ጤንነት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች

## አንቀጽ 13. በሰው አካልና ጤንነት ላይ የሚፈጸም ወንጀል (555-560)

1. በዚህ መመሪያ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 555 - 560 ተከሰው ጥፋተኝነታቸው በፍርድ ቤት በሚረጋገጥባቸው ወንጀል አድራጊዎች ላይ ቅጣት የሚወሰነው ከዚህ ቀጥሎ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ነው፡፡
2. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 555 ‹ታስቦ የሚፈጸም ከባድ የአካል ጉዳት› 558 ‹ከጥፋተኛው ሀሳብ በላይ የደረሰ ጉዳት› እና በወንጀል ሕግ አንቀጽ 559 ንዑስ አንቀጽ 2 ‹በቸልተኝነት የሚፈጸሙ የአካል ጉዳቶች› በወንጀሉ ምክንያት የሚደርሰው የጉዳት ዓይነት እና መጠን ተመሳሳይ በመሆኑ እነዚህን እንደ መስፈርትነት በመጠቀም ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ፤ ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 555 ስድስት ፣ ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 558 ስድስት፤ እና ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 559/2 ሰባት የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡
3. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 556/2 ቀላል የአካል ጉዳት ወንጀልን በተመለከተ በድንጋጌው የተመለከቱትን ማክበጃዎች ማለትም ‹ወንጀሉን ለመፈጸም የተጠቀመበት መሳሪያ›፣ ‹የሙያ ግዴታን በመተላለፍ የተጣሰ መሆኑ›፣ ‹ጉዳት ከደረሰበት ሰው ተጋላጭነት› አንጻር የተቀመጡት መስፈርቶች ለዚህ መመሪያ ሲባል የቅጣት ማክበጃ የሚል ስያሜ ተሰጥቷቸዋል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተመለከቱት የቅጣት ማክበጃዎች ዓይነት ላይ በመመስረት እና ከአንድ በላይ ተደራርበው በሚገኙበት ጊዜ የወንጀል ደረጃውን ከፍ እንዲል በማድረግ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ፤ ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 556/2 አራት የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡
5. የወንጀል ሕግ አንቀጽ 557 ተፈጻሚ የሚሆነው አስቦ ከባድ የአካል ጉዳት (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 555) ወይም ቀላል የአካል ጉዳት (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 556) የማድረስ ወንጀል ሲፈጸም የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ተሟልተው ሲገኙ ብቻ በመሆኑ እና የወንጀል ሕግ አንቀጽ 556/1 ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 557 ያነሰ ቅጣትን ስለሚደነግግ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ፤ ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 555 እና

www.abyssinialaw.com

557 ሰባት እና ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 556/2 እና 557 አምስት የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

6. የወንጀል ሕግ አንቀጽ 556/1፣ 559/1 እና አንቀጽ 560 የያዙት ፍቅድ ሥልጣን ጠባብ በመሆኑ ለእያንዳንዳቸው አንድ የወንጀል ደረጃ ተዘጋጅቷል፡፡

## ታስቦ የሚፈጸም ከባድ የአካል ጉዳት (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 555)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 555 | 1 | የሰውን አካል ወይም አስፈላጊ ከሆኑ ብልቶች ወይም ሕዋሳቶች አንዱን ያጎደለ ወይም እንዳያገለግሉ ያደረገ ወይም ማናቸውንም ሌላ ከባድ የሆነ ጉዳትን በሌላ ሰው ላይ ያደረሰ ከሆነ | 16 |
| 555 | 2 | በሰው አካል ወይም አስፈላጊ ከሆኑ ብልቶች ወይም ሕዋሳቶች ከአንድ በላይ ያጐደለ ወይም እንዳያገለግሉ ያደረገ | 19 |
| 555 | 3 | በሰውነት ወይም በአእምሮ ላይ ለዘወትር ጠንቅ የሚያተርፍ ወይም ከባድ ጉዳት የሚያደርስ በሽታን የሚያስከትል ጉዳት ከሆነ | 22 |
| 555 | 4 | የደረሰው ጉዳት በሚያሰቅቅና ጉልህ ሆኖ በሚታይ ሁኔታ የተጎጂውን መልክ ያበላሸ ከሆነ | 25 |

www.abyssinialaw.com

| | | | |
|---|---|---|---|
| 555 | 5 | የደረሰው ጉዳት ለተጎጂው ህይወት የሚያሰጋ ከሆነ | 28 |
| 555 | 6 | ከላይ ከደረጃ 1-5 ከተጠቀሱት መስፈርቶች ከአንድ በላይ ተደራርበው የተገኙ ከሆነ | 31 |

## ታስቦ የሚፈጸም ከባድ የአካል ጉዳት የቅጣት ማቅለያ ሁኔታዎች (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 555 እና 557)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| 555 እና 557/1 | 1 | የሰውን አካል ወይም አስፈላጊ ከሆኑ ብልቶች ወይም ሕዋሳቶች አንዱን ያጎደለ ወይም እንዳያገለግሉ ያደረገ ወይም ማናቸውንም ሌላ ከባድ የሆነ ጉዳትን በሌላ ሰው ላይ ያደረሰ ከሆነ | 5 | 1 |
| 555 እና 557/1 | 2 | በሰው አካል ወይም አስፈላጊ ከሆኑ ብልቶች ወይም ሕዋሳቶች ከአንድ በላይ ያጐደለ ወይም እንዳያገለግሉ ያደረገ | 6 | 1 |
| 555 እና 557/1 | 3 | በሰውነት ወይም በአእምሮ ላይ ለዘወትር ጠንቅ የሚያተርፍ ወይም ከባድ ጉዳት የሚያደርስ በሽታን የሚያስከትል ጉዳት ከሆነ | 7 | 2 |

www.abyssinialaw.com

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 555 እና 557/1 | 4 | የደረሰው ጉዳት በሚያሰቅቅና ጉልህ ሆኖ በሚታይ ሁኔታ የተጎጂውን መልክ ያበላሸ ከሆነ | 8 | 2 |
| 555 እና 557/1 | 5 | የደረሰው ጉዳት ለተጎጂው ህይወት የሚያሰጋ ከሆነ | 9 | 3 |
| 555 እና 557/1 | 6 | ከላይ ከደረጃ 1-5 ከተጠቀሱት መስፈርቶች ከአንድ በላይ ተደራርበው የተገኙ ከሆነ | 10 | 3 |
| 555 እና 557/2 | 7 | በወንጀል ሕግ አንቀጽ 557/1/ሐ የተመለከተው ተጎጂ በዕድሜው ወይም በአእምሮው ወይም በሌላ ማናቸውም ሁኔታ ጉዳት እንዲደርስበት ያቀረበው ጥያቄ ወይም እሺታው የሚያስከትለውን ነገር በሙሉ ወይም በከፊል ለመረዳት የማይችል ከሆነ | 12 | |

## ታስቦ የሚፈጸም ቀላል የአካል ጉዳት (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 556/1)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| 556/1 | 1 | በሰው አካል ወይም ጤና ላይ አስቦ ቀላል ጉዳት ያደረሰ ከሆነ | 2 | 6 |

www.abyssinialaw.com

## ታስቦ የሚፈጸም ቀላል የአካል ጉዳት (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 556/2)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 556/2 | 1 | በመርዝ ወይም በገዳይ መሣሪያ ወይም የአካል ጉዳት ለማድረስ በሚችል ማናቸውም ሌላ መሣሪያ ቀላል የአካል ወይም የጤና ጉዳት ያደረሰ | 5 |
| 556/2 | 2 | በደረጃ 1 የተመለከተውን ጉዳት ያደረሰው አጥፊ የሙያ ወይም ሌላ ግዴታ የተላለፈ ሰው ከሆነ | 7 |
| 556/2 | 3 | በደረጃ 1 የተመለከተውን ቀላል ጉዳት ያደረሰው በደካማ በሽተኛ ወይም እራሱን ለመከላከል በማይችል ሰው ላይ ከሆነ | 9 |
| 556/2 | 4 | በደካማ፣ በሽተኛ ወይም ራሱን ለመከላከል በማይችል ሰው ላይ ቀላል የአካል ወይም የጤና ጉዳት ያደረሰው አጥፊ የሙያ ወይም ሌላ ግዴታ የተላለፈ ሰው ከሆነ | 11 |

www.abyssinialaw.com

## ታስቦ የሚፈጸም ቀላል የአካል ጉዳት የቅጣት ማቅለያ ሁኔታዎች (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 556/2 እና 557)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| 556(2) እና 557/1 | 1 | በመርዝ ወይም በጎጂ መሣሪያ ወይም የአካል ጉዳት ለማድረስ በሚችል ማናቸውም ሌላ መሣሪያ ቀላል የአካል ወይም የጤና ጉዳት ያደረሰ | 2 | 1 |
| 556(2) እና 557/1 | 2 | በደረጃ 1 የተመለከተውን ጉዳት ያደረሰው አጥፊ የሙያ ወይም ሌላ ግዴታ የተላለፈ ሰው ከሆነ | 4 | 2 |
| 556(2) እና 557/1 | 3 | በደረጃ 1 የተመለከተውን ቀላል ጉዳት ያደረሰው በደካማ በሽተኛ ወይም እራሱን ለመከላከል በማይችል ሰው ላይ ከሆነ | 6 | 2 |
| 556(2) እና 557/1 | 4 | በደካማ፣ በሽተኛ ወይም ራሱን ለመከላከል በማይችል ሰው ላይ ቀላል የአካል ወይም የጤና ጉዳት ያደረሰው አጥፊ የሙያ ወይም ሌላ ግዴታ የተላለፈ ሰው ከሆነ | 8 | 3 |
| 556/2 እና 557/2 | 5 | በወንጀል ሕግ አንቀጽ 557/1/ሐ የተመለከተው ተጎጂ በዕድሜው ወይም በአእምሮው ወይም በሌላ ማናቸውም ሁኔታ ጉዳት እንዲደርስበት ያቀረበውን ጥያቄ ወይም እሺታው የሚያስከትለውን ነገር በሙሉ ወይም በከፊል ለመረዳት የማይችል ከሆነ | 10 | |

www.abyssinialaw.com

## ከጥፋተኛው ሀሳብ በላይ የደረሰ ጉዳት (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 558)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 558 | 1 | የሰውን አካል ወይም አስፈላጊ ከሆኑ ብልቶች ወይም ሕዋሳቶች አንዱን ያጎደለ ወይም እንዳያገለግሉ ያደረገ ወይም ማናቸውንም ሌላ ከባድ የሆነ ጉዳትን በሌላ ሰው ላይ ያደረሰ ከሆነ | 5 |
| 558 | 2 | በሰው አካል ወይም አስፈላጊ ከሆኑ ብልቶች ወይም ሕዋሳቶች ከአንድ በላይ ያጐደለ ወይም እንዳያገለግሉ ያደረገ | 6 |
| 558 | 3 | በሰውነት ወይም በአእምሮ ላይ ለዘወትር ጠንቅ የሚያተርፍ ወይም ከባድ ጉዳት የሚያደርስ በሽታን የሚያስከትል ጉዳት ከሆነ | 7 |
| 558 | 4 | የደረሰው ጉዳት በሚያሰቅቅና ጉልህ ሆኖ በሚታይ ሁኔታ የተጎጂውን መልክ ያበላሸ ከሆነ | 8 |
| 558 | 5 | የደረሰው ጉዳት ለተጎጂው ህይወት የሚያሰጋ ከሆነ | 9 |
| 558 | 6 | ከላይ ከደረጃ 1-5 ከተጠቀሱት መስፈርቶች ከአንድ በላይ ተደራርበው የተገኙ ከሆነ | 11 |

www.abyssinialaw.com

## በቸልተኝነት የሚፈጸሙ የአካል ጉዳቶች (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 559/1)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| 559/1 | 1 | በቸልተኝነት በሌላ ሰው አካል ወይም ጤና ላይ ቀላል ጉዳት ያደረሰ ከሆነ | 4 | 4 |

## በቸልተኝነት የሚፈጸሙ የአካል ጉዳቶች (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 559/2)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| 559/2 | 1 | ቀላል የአካል ወይም የጤና ጉዳት አድራሹ የሌላ ሰውን አካል ወይም ጤንነት የመጠበቅ የሙያ ወይም ሌላ ግዴታ ያለበት እንደ ህክምና ባለሙያ ወይም አሽከርካሪ ያለ ሰው ከሆነ | 7 | 1 |
| 559/2 | 2 | በሰው አካል ወይም አስፈላጊ ከሆኑ ብልቶች ወይም ሕዋሳቶች አንዱን ያጎደለ ወይም እንዳያገለግሉ ያደረገ ከሆነ | 8 | 2 |
| 559/2 | 3 | በሰው አካል ወይም አስፈላጊ ከሆኑ ብልቶች ወይም ሕዋሳቶች ከአንድ በላይ ያጎደለ ወይም እንዳያገለግሉ ያደረገ ከሆነ | 9 | 3 |

www.abyssinialaw.com

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 559/2 | 4 | በሰውነት ወይም በአእምሮ ላይ ለዘወትር ጠንቅ የሚያደርስ ወይም ከባድ ጉዳት የሚያደርስ በሽታን የሚያስከትል ከሆነ | 10 | 4 |
| 559/2 | 5 | የደረሰው ጉዳት በሚያሰቅቅና ጉልህ ሆኖ በሚታይ ሁኔታ የተጎጂውን መልክ ያበላሸ ከሆነ | 11 | 5 |
| 559/2 | 6 | የደረሰው ጉዳት ለተጎጂው ህይወት የሚያሰጋ ከሆነ | 12 | 6 |
| 559/2 | 7 | ከላይ ከደረጃ 1-5 የተጠቀሱት መስፈርቶች ከአንድ በላይ ተደራርበው የተገኙ ከሆነ | 13 | 7 |

## የእጅ እልፊት (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 560/1)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| 560/1 | 1 | የአካል ጉዳትን ወይም የጤና ጉድለትን ሳያደርስ በሌላ ሰው ላይ የእጅ እልፊት ወይም የመጋፋት ድርጊት የፈፀመ ከሆነ | 2 | 1 |

www.abyssinialaw.com

# ርዕስ አምስት

## በሰው ነጻነት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች

### አንቀጽ 14. በሕገ ወጥ መንገድ ኢትዮጵያውያንን ወደ ውጪ ሀገር መላክ (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 598)

1. በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 598 ስር የተደነገገውን ተላልፈው በሕገ ወጥ መንገድ ኢትዮጵያውያንን ለሥራ ወደ ውጪ ሀገር በመላክ ወንጀል ክስ ቀርቦባቸው ጥፋተኛነታቸው በፍርድ ቤት በሚረጋገጥባቸው ወንጀል ፈጻሚዎች ላይ ቅጣት የሚወሰነው ከዚህ ቀጥሎ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ነው፡፡

2. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 598/1 እና 3 ስር የተመለከተውን በመተላለፍ በሕገ ወጥ መንገድ ኢትዮጵያውያንን ለሥራ ወደ ውጪ ሀገር በመላክ ወንጀል ጥፋተኛነታቸው በፍ/ቤት ለሚረጋገጥባቸው አጥፊዎች ያገኙት ጥቅም እና ወንጀሉን ለመፈጸም የተጠቀሟቸው መንገዶች ታሳቢ ተደርገው ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ስድስት የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

3. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 598/1-3 ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ጥፋተኛነታቸው በፍርድ ቤት ለሚረጋገጥባቸው አጥፊዎች ቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች ብቻ ሆነው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 598/2 ስር የተዘረዘሩትን መስፈርቶች በመውሰድ ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 598/1 የወንጀል ደረጃ ለማውጣት ካገለገሉት መለኪያዎች ጋር በማጣመር ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ሰባት የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

4. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 598/3 መሠረት በሕገ ወጥ መንገድ ኢትዮጵያውያንን ወደ ውጪ ሀገር የመላክ ወንጀል ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት ወንዶች ኢትዮጵያውያንንም ስለሚያካትት ለሁለቱም ጾታዎች ተመሳሳይ ደረጃ እና እርከን ተዘጋጅቷል፡፡

5. ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 598 ድንጋጌዎች ደረጃ እና እርከን አወጣጥ የዋሉት መስፈርቶች የተወሰዱት በአዋጅ ቁጥር 737/2004 ከጸደቀው ሕገ ወጥ የሰዎች በተለይም የሴቶችና የህጻናት ዝውውርን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠርና የወንጀሉን ፈጻሚዎች ለመቅጣት ከወጣው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ፕሮቶኮል ነው፡፡

www.abyssinialaw.com

6. በወንጀል ደረጃ መግለጫው ላይ የተበዳዮች (የተጐጂዎች) ቁጥር እና በወንጀል ድርጊቱ ላይ የተገኘው ገንዘብ ወይም ጥቅም በተለያዩ ደረጃዎች ላይ የሚወድቁ በሆነ ጊዜ መነሻ ቅጣት ከፍ ባለ ደረጃ ላይ የሚገኝ ይሆናል፡፡

**በሕገ ወጥ መንገድ ኢትዮጵያውያንን ለሥራ ወደ ውጪ ሀገር መላክ (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 598/1/3)**

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| 598/1/3 | 1 | በወንጀሉ ድርጊቱ የተገኘው ገንዘብ ወይም ጥቅም መጠን ካልተረጋገጠ ወይም ገንዘብ ካልተቀበለ ወይም እስከ ብር 25,000 የተቀበለ ከሆነ | 21 | 3 |
| 598/1/3 | 2 | በወንጀሉ ድርጊት የተገኘው ገንዘብ ወይም ጥቅም ከብር 25,001 እስከ 50, 000 ከሆነ | 22 | 4 |
| 598/1/3 | 3 | በወንጀሉ ድርጊት የተገኘው ገንዘብ ወይም ጥቅም ከብር 50,001 እስከ 75,000 ከሆነ | 23 | 5 |
| 598/1/3 | 4 | በወንጀሉ ድርጊት የተገኘው ገንዘብ ወይም ጥቅም ከብር 75,001-100,000 ከሆነ | 24 | 6 |
| 598/1/3 | 5 | በወንጀሉ ድርጊት የተገኘው ገንዘብ ወይም ጥቅም ከብር 100,000 በላይ ከሆነ | 25 | 7 |
| 598/1/3 | 6 | አጥፊው ተበዳይን በሕገ ወጥ መንገድ ለማዘዋወር ዛቻ ወይም ኃይል ወይም ሌላ የማስገደጃ መንገድ ወይም ጠለፋን ተጠቅሞ ከሆነ | 26 | 7 |

www.abyssinialaw.com

# በሕገ ወጥ መንገድ ኢትዮጵያውያንን ለሥራ ወደ ውጪ ሀገር በመላክ በተበዳይ ሰብአዊ መብት፣ ሕይወት ወይም አካል ላይ ጉዳት እንዲደርስ ማድረግ (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 598/1-3)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| 598/1-3 | 1 | በወንጀሉ ድርጊት የተገኘው ገንዘብ ወይም ጥቅም መጠን ካልተረጋገጠ ወይም ከሌለ ወይም እስከ ብር 25,000 ከሆነ እና የተበዳይ ሰብአዊ መብት ወይም አካል ላይ ጉዳት ከደረሰ | 22 | 4 |
| 598/1-3 | 2 | በወንጀሉ ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ጥቅም ከብር 25,001 - 50,000 ከሆነ እና የተበዳይ ሰብአዊ መብት ወይም አካል ላይ ጉዳት ከደረሰ | 24 | 5 |
| 598/1-3 | 3 | በወንጀሉ ድርጊት የተገኘው ገንዘብ ወይም ጥቅም ከብር 50,001 እስከ 75,000 ከሆነ እና በተበዳይ ሰብአዊ መብት ወይም አካል ላይ ጉዳት ከደረሰ | 26 | 6 |

www.abyssinialaw.com

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 598/1-3 | 4 | በወንጀሉ ድርጊት የተገኘው ገንዘብ ወይም ጥቅም ከብር 75,001 እስከ 100,000 ከሆነ እና በተበዳይ ሰብአዊ መብት ወይም አካል ላይ ጉዳት ከደረሰ | 28 | 7 |
| 598/1-3 | 5 | በወንጀሉ ድርጊት የተገኘው ገንዘብ ወይም ጥቅም ከብር 100,000 በላይ ከሆነ እና በተበዳይ ሰብአዊ መብት ወይም አካል ላይ ጉዳት ከደረሰ | 30 | 8 |
| 598/1-3 | 6 | የተበዳይ ህይወት ያለፈ ከሆነ | 32 | 10 |
| 598/1-3 | 7 | አጥፊው ተበዳይን በህገ ወጥ መንገድ ለማዘዋወር ዛቻ ወይም ሀይል ወይም ሌላ የማስገደጃ መንገድ ወይም ጠለፋን ተጠቅሞ ከሆነ እና የተበዳይ ህይወት ያለፈ ከሆነ | 33 | 10 |

www.abyssinialaw.com

# ርዕስ ስድስት

## በመልካም ፀባይ እና በቤተዘመድ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች

### አንቀጽ 15. በግብረ ሥጋ ነጻነትና ንፅህና ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 620-628)

1. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 620-628 ስር የተደነገገውን በመተላለፍ በግብረ ሥጋ ነጻነትና ንጽህና ላይ በሚፈጸሙ ወንጀሎች ክስ ቀርቦባቸው ጥፋተኛነታቸው በፍርድ ቤት በሚረጋገጥባቸው ተከሳሾች ላይ ቅጣት የሚወሰነው ከዚህ ቀጥሎ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ነው::

2. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 620/1 ስር ለተመለከተው አስገድዶ መድፈር የወንጀሉን አፈጻጸም እና በወንጀል ሕግ አንቀጽ 628 ስር የተመለከቱትን የማክበጃ ምክንያቶች በመጠቀም ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ዘጠኝ የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

3. የወንጀል ሕግ አንቀጽ 620/2 ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 620/1 ማክበጃ ምክንያቶችን በድንጋጌው ከፊደል ሀ-መ ዘርዝሮ ብቻ የያዘ በመሆኑ እና በወንጀል ሕግ አንቀጽ 628 ስር ከተመለከቱት ተጨማሪ የማክበጃ ምክንያቶች ጋር የግድ መጣመር ስላለበት የተበዳይ እና የአጥፊው ማንነት፣ የወንጀሉ አፈጻጸም እና በተበዳይ ላይ የደረሰው ጉዳት ታሳቢ ተደርጎ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ሰባት የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

4. የወንጀል ሕግ አንቀጽ 620/3 ማክበጃ ምክንያቶች ተሟልተው ከተገኙ የሚጣለውን የቅጣት ዓይነት ሕጉ እራሱ ወስኖ ስላስቀመጠው አንድ የወንጀል ደረጃ ብቻ ተዘጋጅቷል፡፡

5. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 621 ስር ለተደነገገው ሴቶች በወንዶች ላይ ለሚፈጽሙት አስገድዶ መድፈር የወንጀሉን አፈጻጸም እና በወንጀል ሕግ አንቀጽ 628 ስር የተመለከቱትን የማክበጃ ምክንያቶች በመጠቀም ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ሰባት የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

6. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 622 ስር ለተመለከተው በንጽህና ክብር ላይ የሚፈጸም የሀይል ድርጊት የወንጀሉን አፈጻጸም እና በወንጀል ሕግ አንቀጽ 628 ስር የተመለከቱትን

www.abyssinialaw.com

ማክበጃ ምክንያቶች በመጠቀም ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ አስር የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

7. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 623 ስር ለተመለከተው አእምሯቸውን በሳቱ ወይም የአእምሮ ደካማ በሆኑ ወይም ለመቃወም በማይችሉ ሰዎች ላይ የሚፈጸም የክብረ ንጽህና ድፍረት በደል የወንጀሉን ዓይነት እና በወንጀል ሕግ አንቀጽ 628 ስር የተመለከቱትን ማክበጃ ምክንያቶች በመጠቀም ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ አስር የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

8. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 624 ስር ለተመለከተው ሆስፒታል ውስጥ በተኙ፣ በተጋዙ ወይም በታሰሩ ሰዎች ላይ የሚፈጸም የክብረ ንጽህና ድፍረት በደል የወንጀሉን ዓይነት እና በወንጀል ሕግ አንቀጽ 628 ስር የተመለከቱትን ማክበጃ ምክንያቶች በመጠቀም ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ አሥር የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

9. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 625 ስር ለተመለከተው አንድ ሴት ያለባትን ከፍ ያለ ችግር ወይም ጥገኝነትዋን ምክንያት በማድረግ የሚፈጸም ድርጊት የወንጀሉን ዓይነት እና በወንጀል ሕግ አንቀጽ 628 ሥር የተመለከቱትን ማክበጃ ምክንያቶች በመጠቀም ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ አሥር የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

10. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 626/1 ሥር ለተመለከተው ዕድሜያቸው አሥራ ሶስት ዓመት በሆነና አስራ ስምንት ዓመት ባልሞላቸው ልጆች ላይ የሚፈጸም የግብረ ሥጋ ድፍረት በደል የተበዳይን የዕድሜ ሁኔታ እና እና በወንጀል ሕግ አንቀጽ 626/4/ሀ እና 628 ስር የተመለከቱትን ማክበጃ ምክንያቶች በመጠቀም ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ አሥር የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

11. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 626/2 ስር ለተመለከተው ዕድሜያቸው አስራ ሶስት ዓመት በሆነና አስራ ስምንት ዓመት ባልሞላቸው ልጆች ላይ የሚፈጸም የግብረ ሥጋ ድፍረት በደል የተበዳይን የዕድሜ ሁኔታ እና በወንጀል ሕግ አንቀጽ 626/4/ለ እና 628 ስር የተመለከቱትን ማክበጃ ምክንያቶች በመጠቀም ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ሰባት የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

12. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 626/3 ስር ለተመለከተው ዕድሜያቸው አስራ ሶስት ዓመት በሆነና አስራ ስምንት ዓመት ባልሞላቸው ልጆች ላይ የሚፈጸም የግብረ ሥጋ ድፍረት

www.abyssinialaw.com

በደል የተበዳይን የዕድሜ ሁኔታ እና በወንጀል ሕግ አንቀጽ 626/4/ሐ እና 628 ስር የተመለከቱትን ማክበጃ ምክንያቶች በመጠቀም ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ አስር የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

13. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 627/1 ስር ለተመለከተው በሕጻናት ልጆች ላይ የሚፈጸም የግብረ ሥጋ ድፍረት በደል የተበዳይን የዕድሜ ሁኔታ እና በወንጀል ሕግ አንቀጽ 627/4/ሀ ስር የተመለከቱትን ማክበጃ ምክንያቶች በመጠቀም ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ አራት ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

14. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 627/2 ስር ለተመለከተው በሕጻናት ልጆች ላይ የሚፈጸም የግብረ ሥጋ ድፍረት በደል የተበዳይን የዕድሜ ሁኔታ እና በወንጀል ሕግ አንቀጽ 627/4/ለ እና 628 ስር የተመለከቱትን ማክበጃ ምክንያቶች በመጠቀም ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ሰባት የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

15. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 627/3 ስር ለተመለከተው በሕጻናት ልጆች ላይ የሚፈጸም የግብረ ሥጋ ድፍረት በደል የተበዳይን የዕድሜ ሁኔታ እና በወንጀል ሕግ አንቀጽ 627/4/ሐ እና 628 ስር የተመለከቱትን ማክበጃ ምክንያቶች በመጠቀም ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ አስር የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

16. የወንጀል ሕግ አንቀጽ 627/5 ማክበጃ ምክንያቶች ተሟልተው ከተገኙ የሚጣለውን የቅጣት ዓይነት ሕጉ እራሱ ወስኖ ስላስቀመጠው አንድ የወንጀል ደረጃ ብቻ ተዘጋጅቷል፡፡

17. አግባብነት ላለው ድንጋጌ የወንጀል ደረጃ ለመለየት የመሳሪያውን አደገኛ መሆን ያለመሆን በተመለከተ ፍርድ ቤቱ በቅድሚያ ምክንያቱን በማስቀመጥ መወሰን አለበት፡፡

www.abyssinialaw.com

## አስገድዶ መድፈር (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 620/1 እና 628)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 620/1 | 1 | አስገድዶ መድፈሩ የተፈጸመው የኃይል ድርጊት በመጠቀም ወይም በብርቱ ዛቻ ወይም ህሊና በማሳት ወይም በሌላ በማናቸውም መንገድ እንደሆነ | 23 |
| 620/1 | 2 | ድርጊቱ በደረጃ 1 ስር የተመለከተው ሆኖ አደገኛ ያልሆነ መሳሪያ የተጠቀመ ከሆነ | 24 |
| 620/1 | 3 | ድርጊቱ በደረጃ 1 ስር የተመለከተው ሆኖ ስለት እና የጦር መሳሪያን የመሳሰለ አደገኛ መሳሪያ ወይም አደንዛዥ ዕጽ የተጠቀመ እንደሆነ | 25 |
| 620/1 እና 628/ለ | 4 | ሞትን በማያስከትል የአባላዘር በሽታ መያዙን እያወቀ አስገድዶ በመድፈር ተበዳይን በበሽታው ያስያዘ እንደሆነ | 27 |
| 620/1 እና 628/ሀ | 5 | በአስገድዶ መድፈሩ ምክንያት ተበዳይ ያረገዘች እንደሆነ | 30 |
| 620/1 እና 628/ሀ፣ለ | 6 | በደረጃ 4 እና 5 ስር የተመለከቱት መስፈርቶች ተደራርበው የተገኙ እንደሆነ | 31 |
| 620/1 እና 628/ለ | 7 | ሞትን በሚያስከትል የአባላዘር በሽታ መያዙን እያወቀ ተበዳይን አስገድዶ በመድፈር በበሽታው ያስያዘ እንደሆነ | 32 |
| 620/1 እና | 8 | በደረጃ 5 እና 7 ስር የተመለከቱት መስፈርቶች ተደራርበው የተገኙ እንደሆነ | 33 |

www.abyssinialaw.com

| | | | |
|---|---|---|---|
| 628/ሀ፣ለ | | | |
| 620/1 እና 628/ሐ | 9 | ተበዳይ በአስገድዶ መድፈሩ ምክንያት በደረሰባት ከባድ ኀዘን ወይም ጭንቀት፣ ሀፍረት ወይም ተስፋ መቁረጥ የተነሳ ራሷን የገደለች እንደሆነ | 34 |

## አስገድዶ መድፈር (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 620/2/ሀ-መ እና 628)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 620/2 | 1 | በድንጋጌው ከፊደል ሀ-ሐ ከተመለከቱት የማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ብቻ ተሟልቶ ሲገኝ | 27 |
| 620/2 እና 628/ለ | 2 | በወንጀል ሕግ አንቀጽ 620/2 ስር ከፊደል ሀ-ሐ ከተመለከቱት የማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ብቻ ተሟልቶ ሲገኝ እና ሞትን በማያስከትል የአባላዘር በሽታ መያዙን እያወቀ በግብረ ሥጋ ግንኙነቱ ተበዳይን በበሽታው ያስያዘ እንደሆነ | 29 |
| 620/2 | 3 | በወንጀል ሕግ አንቀጽ 620/2 ስር ከፊደል ሀ-ሐ ከተመለከቱት የማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ ሁለቱ ተሟልተው ሲገኙ | 30 |
| 620/2 እና 628/ሀ | 4 | በወንጀል ሕግ አንቀጽ 620/2 ስር ከፊደል ሀ-ሐ ከተመለከቱት የማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ ሦስቱም ተሟልተው ሲገኙ ወይም አንዱ ብቻ ተሟልቶ ሲገኝ እና | 32 |

www.abyssinialaw.com

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | በአስገድዶ መድፈሩ ምክንያት ተበዳይ ያረገዘች እንደሆነ ወይም በድንጋጌው በፊደል መ ስር ከተመለከቱት የማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ተሟልቶ ሲገኝ | |
| 620/2 እና 628/ለ | 5 | በድንጋጌው ከፊደል ሀ-መ ስር ከተመለከቱት የማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ብቻ ተሟልቶ ሲገኝ እና ሞትን በሚያስከትል የአባላዘር በሽታ መያዙን እያወቀ ተበዳይን አስገድዶ በመድፈር በበሽታው ያስያዘ እንደሆነ | 34 |
| 620/2 | 6 | በድንጋጌው ከፊደል ሀ-መ ስር ከተመለከቱት የማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ አራቱም ተሟልተው የተገኙ እንደሆነ | 35 |
| 620/2 እና 628/ሐ | 7 | በድንጋጌው ከፊደል ሀ-መ ከተመለከቱት የማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ብቻ ተሟልቶ ሲገኝ እና ተበዳይ በአስገድዶ መድፈሩ ምክንያት በደረሰባት ከባድ ኀዘን ወይም ጭንቀት፣ ሀፍረት ወይም ተስፋ መቁረጥ የተነሳ ራሷን የገደለች እንደሆነ | 36 |

## አስገድዶ መድፈር (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 620/3)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 620/3 | 1 | አስገድዶ መድፈሩ ከባድ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳትን ወይም ሞትን ያስከተለ እንደሆነ | 38 |

www.abyssinialaw.com

# አስገድዶ መድፈር (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 621 እና 628)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 621 | 1 | አስገድዶ መድፈሩ የተፈጸመው የኃይል ድርጊት በመጠቀም ወይም በብርቱ ዛቻ ወይም ህሊና በማሳት ወይም በሌላ በማናቸውም መንገድ እንደሆነ | 7 |
| 621 | 2 | ተበዳይን አስገድዶ ለመድፈር አደገኛ ያልሆነ መሳሪያ የተጠቀመች እንደሆነ | 8 |
| 621 | 3 | ተበዳይን አስገድዶ ለመድፈር ስለት እና የጦር መሳሪያን የመሳሰለ አደገኛ መሳሪያ ወይም አደንዛዥ ዕጽ የተጠቀመች እንደሆነ | 9 |
| 621 | 4 | አስገድዶ መድፈሩ በተበዳይ ላይ ከባድ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳትን አስከትሎ እንደሆነ | 14 |
| 621 እና 628/ለ | 5 | ሞትን በማያስከትል የአባላዘር በሽታ መያዟን እያወቀች አስገድዶ በመድፈር ተበዳይን በበሽታው ያስያዘች እንደሆነ | 24 |
| 621 እና 628/ለ | 6 | ሞትን በሚያስከትል የአባላዘር በሽታ መያዟን እያወቀች ተበዳይን አስገድዶ በመድፈር በበሽታው ያስያዘች እንደሆነ | 32 |
| 621 እና 628/ሐ | 7 | ተበዳይ በአስገድዶ መድፈሩ ምክንያት በደረሰበት ከባድ ኀዘን ወይም ጭንቀት፣ ሀፍረት ወይም ተስፋ መቁረጥ የተነሳ ራሱን የገደለ እንደሆነ | 34 |

www.abyssinialaw.com

## በንጽህና ክብር ላይ የሚፈጸም የሀይል ድርጊት (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 622 እና 628)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 622 | 1 | የግብረ ሥጋ መሰል ተግባሩ ወይም ማናቸውም ሌላ ዓይነት ለንጽህና ክብር ተቃራኒ የሆነው ድርጊት የተፈጸመው የኃይል ድርጊት በመጠቀም ወይም በብርቱ ዛቻ ወይም ህሊና በማሳት ወይም በሌላ በማናቸውም መንገድ እንደሆነ | 7 |
| 622 | 2 | ድርጊቱ በደረጃ 1 ስር የተመለከተው ሆኖ የተፈጸመው አደገኛ ያልሆነ መሳሪያ በመጠቀም እንደሆነ | 9 |
| 622 | 3 | ድርጊቱ በደረጃ 1 ስር የተመለከተው ሆኖ የተፈጸመው ስለት እና የጦር መሳሪያን የመሳሰለ አደገኛ መሳሪያ ወይም አደንዛዥ ዕጽ በመጠቀም እንደሆነ | 19 |
| 622 | 4 | ድርጊቱ በተበዳይ ላይ ከባድ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳትን አስከትሎ እንደሆነ | 23 |
| 622 እና 628/ለ | 5 | ሞትን በማያስከትል የአባላዘር በሽታ መያዙን እያወቀ የግብረ ሥጋ ግንኙነትን በመሰለ ድርጊት ወይም ለንጽህና ክብር ተቃራኒ በሆነ ማናቸውም ሌላ ዓይነት ድርጊት ተበዳይን በበሽታው ያስያዘ እንደሆነ | 24 |

www.abyssinialaw.com

| | | | |
|---|---|---|---|
| 622 እና 628/ሀ | 6 | የግብረ ሥጋ ግንኙነትን በመሰለ ድርጊት ወይም ለንጽህና ክብር ተቃራኒ በሆነ ማናቸውም ሌላ ዓይነት ድርጊት ምክንያት ተበዳይ ያረገዘች እንደሆነ | 30 |
| 622 እና 628/ለ | 7 | በደረጃ 5 እና 6 ስር የተመለከቱት መስፈርቶች ተደራርበው የተገኙ እንደሆነ | 31 |
| 622 እና 628/ሐ | 8 | ሞትን በሚያስከትል የአባላዘር በሽታ መያዙን እያወቀ ከተበዳይ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነትን የመሰለ ድርጊት ወይም ለንጽህና ክብር ተቃራኒ የሆነ ማናቸውንም ሌላ ዓይነት ድርጊት በመፈጸም በበሽታው ያስያዘ እንደሆነ | 32 |
| 622 እና 628/ለ | 9 | በደረጃ 6 እና 8 ስር የተመለከቱት መስፈርቶች ተደራርበው የተገኙ እንደሆነ | 33 |
| 622 እና 628/ሐ | 10 | ተበዳይ የግብረ ሥጋ ግንኙነትን በመሰለ ድርጊት ወይም ለንጽህና ክብር ተቃራኒ በሆነ ማናቸውም ሌላ ዓይነት ድርጊት ምክንያት በደረሰበት ከባድ ኀዘን ወይም ጭንቀት፣ ሀፍረት ወይም ተስፋ መቁረጥ የተነሳ ራሱን የገደለ እንደሆነ | 34 |

www.abyssinialaw.com

## አእምሯቸውን በሳቱ ወይም በአእምሮ ደካማ በሆኑ ወይም ለመቃወም በማይችሉ ሰዎች ላይ የሚፈጸም የክብረ ንጽህና ድፍረት በደል (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 623 እና 628)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 623 | 1 | ድንጋጌውን በመተላለፍ የተፈጸመው የወንጀል ድርጊት የግብረ ሥጋ ግንኙነት መሰል ወይም ሌላ ለመልካም ጸባይ ተቃራኒ የሆነ ተግባር እንደሆነ | 7 |
| 623 | 2 | ድንጋጌውን በመተላለፍ የተፈጸመው የወንጀል ድርጊት የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንደሆነ | 14 |
| 623 | 3 | ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ በተበዳይ ላይ ከባድ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳትን አስከትሎ እንደሆነ | 18 |
| 623 | 4 | ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ በተበዳይ ላይ ከባድ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳትን አስከትሎ እንደሆነ | 23 |
| 623 እና 628/ለ | 5 | ሞትን በማያስከትል የአባላዘር በሽታ መያዙን እያወቀ በግብረ ሥጋ ግንኙነት ወይም የግብረ ሥጋ ግንኙነትን በመሰለ ድርጊት ወይም ለንጽህና ክብር ተቃራኒ በሆኑ ማናቸውም ሌላ ዓይነት ድርጊት ተበዳይን በበሽታው ያስያዘ እንደሆነ | 24 |

www.abyssinialaw.com

| | | | |
|---|---|---|---|
| 623 እና 628/ሀ | 6 | በግብረ ሥጋ ግንኙነት ወይም የግብረ ሥጋ ግንኙነትን በመሰለ ድርጊት ወይም ለንጽህና ክብር ተቃራኒ በሆነ ማናቸውም ሌላ ዓይነት ድርጊት ምክንያት ተበዳይ ያረገዘች እንደሆነ | 30 |
| 623 እና 628/ለ | 7 | በደረጃ 5 እና 6 ስር የተመለከቱት መስፈርቶች ተደራርበው የተገኙ እንደሆነ | 31 |
| 623 እና 628/ሐ | 8 | ሞትን በሚያስከትል የአባላዘር በሽታ መያዙን እያወቀ ከተበዳይ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ወይም የግብረ ሥጋ ግንኙነትን የመሰለ ድርጊት ወይም ለንጽህና ክብር ተቃራኒ የሆነ ማናቸውንም ሌላ ዓይነት ድርጊት በመፈጸም በበሽታው ያስያዘ እንደሆነ | 32 |
| 623 እና 628/ለ | 9 | በደረጃ 6 እና 8 ስር የተመለከቱት መስፈርቶች ተደራርበው የተገኙ እንደሆነ | 33 |
| 623 እና 628/ሐ | 10 | ተበዳይ በግብረ ሥጋ ግንኙነት ወይም የግብረ ሥጋ ግንኙነትን በመሰለ ድርጊት ወይም ለንጽህና ክብር ተቃራኒ በሆነ ማናቸውም ሌላ ዓይነት ድርጊት ምክንያት በደረሰበት ከባድ ኀዘን ወይም ጭንቀት፣ ሀፍረት ወይም ተስፋ መቁረጥ የተነሳ ራሱን የገደለ እንደሆነ | 34 |

www.abyssinialaw.com

## ሆስፒታል ውስጥ በተኙ፣ በተጋዙ ወይም በታሰሩ ሰዎች ላይ የሚፈጸም የክብረ ንጽህና ድፍረት በደል (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 624 እና 628)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 624 | 1 | ድንጋጌውን በመተላለፍ የተፈጸመው የወንጀል ድርጊት የግብረ ሥጋ ግንኙነት መሰል ወይም ሌላ ለመልካም ጸባይ ተቃራኒ የሆነ ተግባር እንደሆነ | 7 |
| 624 | 2 | ድንጋጌውን በመተላለፍ የተፈጸመው የወንጀል ድርጊት የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንደሆነ | 14 |
| 624 | 3 | ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ በተበዳይ ላይ ከባድ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳትን አስከትሎ እንደሆነ | 18 |
| 624 | 4 | ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ በተበዳይ ላይ ከባድ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳትን አስከትሎ እንደሆነ | 23 |
| 624 እና 628/ለ | 5 | ሞትን በማያስከትል የአባላዘር በሽታ መያዙን እያወቀ በግብረ ሥጋ ግንኙነት ወይም የግብረ ሥጋ ግንኙነትን በመሰለ ድርጊት ወይም ለንጽህና ክብር ተቃራኒ በሆነ ማናቸውም ሌላ ዓይነት ድርጊት ተበዳይን በበሽታው ያስያዘ እንደሆነ | 24 |
| 624 እና | 6 | በግብረ ሥጋ ግንኙነት ወይም የግብረ ሥጋ ግንኙነትን በመሰለ ድርጊት ወይም ለንጽህና ክብር ተቃራኒ በሆነ | 30 |

www.abyssinialaw.com

| | | | |
|---|---|---|---|
| 628/ሀ | | ማናቸውም ሌላ ዓይነት ድርጊት ምክንያት ተበዳይ ያረገዘች እንደሆነ | |
| 624 እና 628/ለ | 7 | በደረጃ 5 እና 6 ስር የተመለከቱት መስፈርቶች ተደራርበው የተገኙ እንደሆነ | 31 |
| 624 እና 628/ሐ | 8 | ሞትን በሚያስከትል የአባላዘር በሽታ መያዙን እያወቀ ከተበዳይ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ወይም የግብረ ሥጋ ግንኙነትን የመሰለ ድርጊት ወይም ለንጽህና ክብር ተቃራኒ የሆነ ማናቸውንም ሌላ ዓይነት ድርጊት በመፈጸም በበሽታው ያስያዘ እንደሆነ | 32 |
| 624 እና 628/ለ | 9 | በደረጃ 6 እና 8 ስር የተመለከቱት መስፈርቶች ተደራርበው የተገኙ እንደሆነ | 33 |
| 624 እና 628/ሐ | 10 | ተበዳይ በግብረ ሥጋ ግንኙነት ወይም የግብረ ሥጋ ግንኙነትን በመሰለ ድርጊት ወይም ለንጽህና ክብር ተቃራኒ በሆነ ማናቸውም ሌላ ዓይነት ድርጊት ምክንያት በደረሰበት ከባድ ኀዘን ወይም ጭንቀት፣ ሀፍረት ወይም ተስፋ መቁረጥ የተነሳ ራሱን የገደለ እንደሆነ | 34 |

www.abyssinialaw.com

## አንድ ሴት ያለባትን ከፍ ያለ ችግር ወይም ጥገኝነትዋን ምክንያት በማድረግ የሚፈጸም ድርጊት (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 625 እና 628)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 625 | 1 | ድንጋጌውን በመተላለፍ የተፈጸመው የወንጀል ድርጊት የግብረ ሥጋ ግንኙነት መሰል ወይም ሌላ ለመልካም ጸባይ ተቃራኒ የሆነ ተግባር እንደሆነ | 7 |
| 625 | 2 | ድንጋጌውን በመተላለፍ የተፈጸመው የወንጀል ድርጊት የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንደሆነ | 9 |
| 625 | 3 | ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ በተበዳይ ላይ ከባድ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳትን አስከትሎ እንደሆነ | 11 |
| 625 | 4 | ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ በተበዳይ ላይ ከባድ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳትን አስከትሎ እንደሆነ | 13 |
| 625 እና 628/ለ | 5 | ሞትን በማያስከትል የአባላዘር በሽታ መያዙን እያወቀ በግብረ ሥጋ ግንኙነት ወይም የግብረ ሥጋ ግንኙነትን በመሰለ ድርጊት ወይም ለንጽህና ክብር ተቃራኒ በሆነ ማናቸውም ሌላ ዓይነት ድርጊት ተበዳይን በበሽታው ያስያዘ እንደሆነ | 24 |
| 625 እና | 6 | በግብረ ሥጋ ግንኙነት ወይም የግብረ ሥጋ ግንኙነትን በመሰለ ድርጊት ወይም ለንጽህና ክብር ተቃራኒ በሆነ | 30 |

www.abyssinialaw.com

| | | | |
|---|---|---|---|
| 628/ሀ | | ማናቸውም ሌላ ዓይነት ድርጊት ምክንያት ተበዳይ ያረገዘች እንደሆነ | |
| 625 እና 628/ለ | 7 | በደረጃ 5 እና 6 ስር የተመለከቱት መስፈርቶች ተደራርበው የተገኙ እንደሆነ | 31 |
| 625 እና 628/ሐ | 8 | ሞትን በሚያስከትል የአባላዘር በሽታ መያዙን እያወቀ ከተበዳይ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ወይም የግብረ ሥጋ ግንኙነትን የመሰለ ድርጊት ወይም ለንጽህና ክብር ተቃራኒ የሆነ ማናቸውንም ሌላ ዓይነት ድርጊት በመፈጸም በበሽታው ያስያዘ እንደሆነ | 32 |
| 625 እና 628/ለ | 9 | በደረጃ 6 እና 8 ስር የተመለከቱት መስፈርቶች ተደራርበው የተገኙ እንደሆነ | 33 |
| 625 እና 628/ሐ | 10 | ተበዳይ በግብረ ሥጋ ግንኙነት ወይም የግብረ ሥጋ ግንኙነትን በመሰለ ድርጊት ወይም ለንጽህና ክብር ተቃራኒ በሆነ ማናቸውም ሌላ ዓይነት ድርጊት ምክንያት በደረሰባት ከባድ ኀዘን ወይም ጭንቀት፣ ሀፍረት ወይም ተስፋ መቁረጥ የተነሳ ራሷን የገደለች እንደሆነ | 34 |

www.abyssinialaw.com

## ዕድሜያቸው አስራ ሶስት ዓመት በሆነና አስራ ስምንት ዓመት ባልሞላቸው ልጆች ላይ የሚፈጸም የግብረ ሥጋ ድፍረት በደል (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 626/1፣ 626/4/ሀ እና 628)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 626/1 | 1 | የግብረ ሥጋ ግንኙነቱ የተፈጸመው ዕድሜዋ 16 ዓመት ከሞላት እና አስራ ስምንት ዓመት ካልሞላት ሴት ህጻን ልጅ ጋር እንደሆነ | 16 |
| 626/1 | 2 | የግብረ ሥጋ ግንኙነቱ የተፈጸመው ዕድሜዋ 13 ዓመት ከሞላት እና አስራ ስድስት ዓመት ካልሞላት ሴት ህጻን ልጅ ጋር እንደሆነ | 17 |
| 626/1 እና 626/4/ሀ | 3 | በደረጃ 1 የተመለከተችው ተበዳይ የጥፋተኛው ተማሪ፣ የሙያ መለማመጃ ትምህርት ተማሪ፣ የቤት ሠራተኛ፣ ወይም ጥፋተኛው በሞግዚትነት የሚያሳድጋት ልጅ፣ ወይም እንዲጠብቃት ወይም እንዲንከባከባት በአደራ የተሰጠችው ልጅ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ በቀጥታ በእርሱ ጥገኝነት ወይም ቁጥጥር ሥር የምትገኝ ልጅ እንደሆነች | 21 |
| 626/1 እና 626/4/ሀ | 4 | በደረጃ 2 የተመለከተችው ተበዳይ የጥፋተኛው ተማሪ፣ የሙያ መለማመጃ ትምህርት ተማሪ፣ የቤት ሠራተኛ፣ ወይም ጥፋተኛው በሞግዚትነት የሚያሳድጋት ልጅ፣ ወይም እንዲጠብቃት ወይም እንዲንከባከባት በአደራ የተሰጠችው ልጅ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ በቀጥታ በእርሱ ጥገኝነት ወይም ቁጥጥር ሥር የምትገኝ | 22 |

www.abyssinialaw.com

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ልጅ እንደሆነች | |
| 626/1 እና 628/ለ | 5 | ሞትን በማያስከትል የአባላዘር በሽታ መያዙን እያወቀ በግብረ ሥጋ ግንኙነቱ ተበዳይን በበሽታው ያስያዘ እንደሆነ | 24 |
| 626/1 እና 628/ሀ | 6 | በግብረ ሥጋ ግንኙነቱ ምክንያት ተበዳይ ያረገዘች እንደሆነ | 30 |
| 626/1 እና 628/ለ | 7 | በደረጃ 5 እና 6 ስር የተመለከቱት መስፈርቶች ተደራርበው የተገኙ እንደሆነ | 31 |
| 626/1 እና 628/ሐ | 8 | ሞትን በሚያስከትል የአባላዘር በሽታ መያዙን እያወቀ ከተበዳይ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት በመፈጸም በበሽታው ያስያዘ እንደሆነ | 32 |
| 626/1 እና 628/ለ | 9 | በደረጃ 6 እና 8 ስር የተመለከቱት መስፈርቶች ተደራርበው የተገኙ እንደሆነ | 33 |
| 626/1 እና 628/ሐ | 10 | ተበዳይ በግብረ ሥጋ ግንኙነቱ ምክንያት በደረሰባት ከባድ ኀዘን ወይም ጭንቀት፣ ሀፍረት ወይም ተስፋ መቁረጥ የተነሳ ራሷን የገደለች እንደሆነ | 34 |

www.abyssinialaw.com

## ዕድሜያቸው አስራ ሶስት ዓመት በሆነና አስራ ስምንት ዓመት ባልሞላቸው ልጆች ላይ የሚፈጸም የግብረ ሥጋ ድፍረት በደል (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 626/2፣ 626/4/ለ እና 628)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 626/2 | 1 | የግብረ ሥጋ ግንኙነቱ የተፈጸመው ዕድሜው አስራ ስድስት ዓመት ከሞላውና እና አስራ ስምንት ዓመት ካልሞላው ወንድ ህጻን ልጅ ጋር እንደሆነ | 7 |
| 626/2 | 2 | የግብረ ሥጋ ግንኙነቱ የተፈጸመው እድሜው አስራ ሶስት ዓመት ከሞላውና እና አስራ ስድስት ዓመት ካልሞላው ወንድ ህጻን ልጅ ጋር እንደሆነ | 8 |
| 626/2 እና 626/4/ለ | 3 | በደረጃ 1 የተመለከተው ተበዳይ የጥፋተኛዋ ተማሪ፣ የሙያ መለማመጃ ትምህርት ተማሪ፣ የቤት ሠራተኛ፣ ወይም ጥፋተኛዋ በሞግዚትነት የምታሳድገው ልጅ፣ ወይም እንድትጠብቀው ወይም እንድትንከባከበው በአደራ የተሰጣት ልጅ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ በቀጥታ በእርሷ ጥገኝነት ወይም ቁጥጥር ሥር የሚገኝ ልጅ እንደሆነ | 16 |
| 626/2 እና 626/4/ለ | 4 | በደረጃ 2 የተመለከተው ተበዳይ የጥፋተኛዋ ተማሪ፣ የሙያ መለማመጃ ትምህርት ተማሪ፣ የቤት ሠራተኛ፣ ወይም ጥፋተኛዋ በሞግዚትነት የምታሳድገው ልጅ፣ ወይም እንድትጠብቀው ወይም እንድትንከባከበው በአደራ የተሰጣት ልጅ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ በቀጥታ | 18 |

www.abyssinialaw.com

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | በእርሷ ጥገኝነት ወይም ቁጥጥር ሥር የሚገኝ ልጅ እንደሆነ | |
| 626/2 እና 628/ለ | 5 | ሞትን በማያስከትል የአባላዘር በሽታ መያዟን እያወቀች በግብረ ሥጋ ግንኙነቱ ተበዳይን በበሽታው ያስያዘች እንደሆነ | 24 |
| 626/2 እና 628/ለ | 6 | ሞትን በሚያስከትል የአባላዘር በሽታ መያዟን እያወቀች ተበዳይን ግብረ ሥጋ ግንኙነትን የመሰለ ወይም ለንጽህና ክብር ተቃራኒ የሆነ ነገር እንዲፈጽም በማድረግ በበሽታው ያስያዘች እንደሆነ | 32 |
| 626/2 እና 628/ሐ | 7 | ተበዳይ የግብረ ሥጋ ግንኙነትን በመሰለው ድርጊት ወይም ለንጽህና ክብር ተቃራኒ በሆነው ድርጊት ምክንያት በደረሰበት ከባድ ኀዘን ወይም ጭንቀት፣ ሀፍረት ወይም ተስፋ መቁረጥ የተነሳ ራሱን የገደለ እንደሆነ | 34 |

**ዕድሜያቸው አስራ ሶስት ዓመት በሆነና አስራ ስምንት ዓመት ባልሞላቸው ልጆች ላይ የሚፈጸም የግብረ ሥጋ ድፍረት በደል (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 626/3፣ 626/4/ሐ እና 628)**

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 626/3 | 1 | የግብረ ሥጋ ግንኙነትን የመሰለ ድርጊት ወይም ለንጽህና ክብር ተቃራኒ የሆነው ማናቸውም ሌላ ዓይነት ድርጊቱ የተፈጸመው ዕድሜው 16 ዓመት ከሞላውና እና አስራ ስምንት ዓመት ካልሞላው ህጻን ልጅ ጋር እንደሆነ | 3 |

www.abyssinialaw.com

| | | | |
|---|---|---|---|
| 626/3 | 2 | የግብረ ሥጋ ግንኙነትን የመሰለ ድርጊት ወይም ለንጽህና ክብር ተቃራኒ የሆነው ማናቸውም ሌላ ዓይነት ድርቱ የተፈጸመው ዕድሜው አስራ ሦስት ዓመት ከሞላውና አስራ ስድስት ዓመት ካልሞላው ህጻን ልጅ ጋር እንደሆነ | 5 |
| 626/3 እና 626/4/ሐ | 3 | በደረጃ 1 የተመለከተው ተበዳይ የጥፋተኛው ተማሪ፣ የሙያ መለማመጃ ትምህርት ተማሪ፣ የቤት ሠራተኛ፣ ወይም ጥፋተኛው በሞግዚትነት የሚያሳድገው ልጅ፣ ወይም እንዲጠብቀው ወይም እንዲንከባከበው በአደራ የተሰጠው ልጅ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ በቀጥታ በእርሱ ጥገኝነት ወይም ቁጥጥር ሥር የሚገኝ ልጅ ከሆነ | 7 |
| 626/3 እና 626/4/ሐ | 4 | በደረጃ 2 የተመለከተው ተበዳይ የጥፋተኛው ተማሪ፣ የሙያ መለማመጃ ትምህርት ተማሪ፣ የቤት ሠራተኛ፣ ወይም ጥፋተኛው በሞግዚትነት የሚያሳድገው ልጅ፣ ወይም እንዲጠብቀው ወይም እንዲንከባከበው በአደራ የተሰጠው ልጅ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ በቀጥታ በእርሱ ጥገኝነት ወይም ቁጥጥር ሥር የሚገኝ ልጅ እንደሆነ | 9 |
| 626/3 እና 628/ለ | 5 | ሞትን በማያስከትል የአባላዘር በሽታ መያዙን እያወቀ የግብረ ሥጋ ግንኙነትን በመሰለ ድርጊት ወይም ለንጽህና ክብር ተቃራኒ በሆነ ማናቸውም ሌላ ዓይነት ድርጊት ተበዳይን በበሽታው ያስያዘ እንደሆነ | 24 |
| 626/3 እና 628/ሀ | 6 | የግብረ ሥጋ ግንኙነትን በመሰለ ድርጊት ወይም ለንጽህና ክብር ተቃራኒ በሆነ ማናቸውም ሌላ ዓይነት ድርጊት ምክንያት ተበዳይ ያረገዘች እንደሆነ | 30 |
| 626/3 እና | 7 | በደረጃ 5 እና 6 ስር የተመለከቱት መስፈርቶች ተደራርበው የተገኙ እንደሆነ | 31 |

www.abyssinialaw.com

| | | | |
|---|---|---|---|
| 628/ለ | | | |
| 626/3 እና 628/ሐ | 8 | ሞትን በሚያስከትል የአባላዘር በሽታ መያዙን እያወቀ ከተበዳይ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነትን የመሰለ ድርጊት ወይም ለንጽህና ክብር ተቃራኒ በሆነ ማናቸውንም ሌላ ዓይነት ድርጊት በመፈጸም በበሽታው ያስያዘ እንደሆነ | 32 |
| 626/3 እና 628/ለ | 9 | በደረጃ 6 እና 8 ስር የተመለከቱት መስፈርቶች ተደራርበው የተገኙ እንደሆነ | 33 |
| 626/3 እና 628/ሐ | 10 | ተበዳይ የግብረ ሥጋ ግንኙነትን በመሰለ ድርጊት ወይም ለንጽህና ክብር ተቃራኒ በሆነ ማናቸውም ሌላ ዓይነት ድርጊት ምክንያት በደረሰበት ከባድ ኀዘን ወይም ጭንቀት፣ ሀፍረት ወይም ተስፋ መቁረጥ የተነሳ ራሱን የገደለ እንደሆነ | 34 |

## በሕጻናት ልጆች ላይ የሚፈጸም የግብረ ሥጋ ድፍረት በደል (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 627/1 እና 627/4/ሀ)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 627/1 | 1 | ዕድሜዋ ዘጠኝ ዓመት ከሞላት እና አስራ ሶስት ዓመት ካልሞላት ሴት ህጻን ልጅ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት የፈጸመ ወይም ህጻኗ እንዲህ ዓይነቱን ድርጊት ከእርሱ ጋር እንደትፈጽም ያደረገ እንደሆነ | 34 |

www.abyssinialaw.com

| | | | |
|---|---|---|---|
| 627/1 | 2 | ዕድሜዋ ዘጠኝ ዓመት ካልሞላት ሴት ህጻን ልጅ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት የፈጸመ ወይም ህጻኗ እንዲህ ዓይነቱን ድርጊት ከእርሱ ጋር እንድትፈጽም ያደረገ እንደሆነ | 35 |
| 627/1 እና 627/4/ሀ | 3 | በደረጃ 1 የተመለከተችው ተበዳይ የጥፋተኛው ተማሪ፣ የሙያ መለማመጃ ትምህርት ተማሪ፣ የቤት ሠራተኛ፣ ወይም ጥፋተኛው በሞግዚትነት የሚያሳድጋት ልጅ፣ ወይም እንዲጠብቃት ወይም እንዲንከባከባት በአደራ የተሰጠችው ልጅ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ በቀጥታ በእርሱ ጥገኝነት ወይም ቁጥጥር ሥር የምትገኝ ልጅ እንደሆነች | 36 |
| 627/1 እና 627/4/ሀ | 4 | በደረጃ 2 የተመለከተችው ተበዳይ የጥፋተኛው ተማሪ፣ የሙያ መለማመጃ ትምህርት ተማሪ፣ የቤት ሠራተኛ፣ ወይም ጥፋተኛው በሞግዚትነት የሚያሳድጋት ልጅ፣ ወይም እንዲጠብቃት ወይም እንዲንከባከባት በአደራ የተሰጠችው ልጅ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ በቀጥታ በእርሱ ጥገኝነት ወይም ቁጥጥር ሥር የምትገኝ ልጅ እንደሆነች | 37 |

www.abyssinialaw.com

## በሕጻናት ልጆች ላይ የሚፈጸም የግብረ ሥጋ ድፍረት በደል (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 627/2 እና 627/4/ለ)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 627/2 | 1 | የግብረ ሥጋ ግንኙነቱ የተፈጸመው ዕድሜው ዘጠኝ ዓመት ከሞላው እና አስራ ሦስት ዓመት ካልሞላው ወንድ ህጻን ልጅ ጋር እንደሆነ | 7 |
| 627/2 | 2 | የግብረ ሥጋ ግንኙነቱ የተፈጸመው ዕድሜው ዘጠኝ ዓመት ካልሞላው ወንድ ህጻን ልጅ ጋር እንደሆነ | 8 |
| 627/2 እና 627/4/ለ | 3 | በደረጃ 1 የተመለከተው ተበዳይ የጥፋተኛዋ ተማሪ፣ የሙያ መለማመጃ ትምህርት ተማሪ፣ የቤት ሠራተኛ፣ ወይም ጥፋተኛዋ በሞግዚትነት የምታሳድገው ልጅ፣ ወይም እንድትጠብቀው ወይም እንድትንከባከበው በአደራ የተሰጣት ልጅ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ በቀጥታ በእርሷ ጥገኝነት ወይም ቁጥጥር ሥር የሚገኝ ልጅ እንደሆነ | 16 |
| 627/2 እና 627/4/ለ | 4 | በደረጃ 2 የተመለከተው ተበዳይ የጥፋተኛዋ ተማሪ፣ የሙያ መለማመጃ ትምህርት ተማሪ፣ የቤት ሠራተኛ፣ ወይም ጥፋተኛዋ በሞግዚትነት የምታሳድገው ልጅ፣ ወይም እንድትጠብቀው ወይም እንድትንከባከበው በአደራ የተሰጣት ልጅ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ በቀጥታ በእርሷ ጥገኝነት ወይም ቁጥጥር ሥር የሚገኝ ልጅ እንደሆነ | 18 |

www.abyssinialaw.com

| | | | |
|---|---|---|---|
| 627/2 እና 628/ለ | 5 | ሞትን በማያስከትል የአባላዘር በሽታ መያዟን እያወቀች በግብረ ሥጋ ግንኙነቱ ተበዳይን በበሽታው ያስያዘች እንደሆነ | 24 |
| 627/2 እና 628/ለ | 6 | ሞትን በሚያስከትል የአባላዘር በሽታ መያዟን እያወቀች ከተበዳይ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት በመፈጸም በበሽታው ያስያዘች እንደሆነ | 32 |
| 627/2 እና 628/ሐ | 7 | ተበዳይ በግብረ ሥጋ ግንኙነቱ ምክንያት በደረሰበት ከባድ ኀዘን ወይም ጭንቀት፣ ሀፍረት ወይም ተስፋ መቁረጥ የተነሳ ራሱን የገደለ እንደሆነ | 34 |

## በሕጻናት ልጆች ላይ የሚፈጸም የግብረ ሥጋ ድፍረት በደል (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 627/3፣ 627/4/ሐ እና 628)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 627/3 | 1 | የግብረ ሥጋ ግንኙነትን የመሰለ ድርጊት ወይም ለንጽህና ክብር ተቃራኒ የሆነው ማናቸውም ሌላ ዓይነት ድርጊቱ የተፈጸመው ዕድሜው ዘጠኝ ዓመት ከሞላውና እና አስራ ሦስት ዓመት ካልሞላው ህጻን ልጅ ጋር እንደሆነ | 7 |
| 627/3 | 2 | የግብረ ሥጋ ግንኙነትን የመሰለ ድርጊት ወይም ለንጽህና ክብር ተቃራኒ የሆነው ማናቸውም ሌላ ዓይነት ድርጊቱ የተፈጸመው ዕድሜው ዘጠኝ ዓመት ካልሞላው ህጻን ልጅ ጋር እንደሆነ | 9 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 627/3 እና 627/4/ሐ | 3 | በደረጃ 1 የተመለከተው ተበዳይ የጥፋተኛው ተማሪ፣ የሙያ መለማመጃ ትምህርት ተማሪ፣ የቤት ሠራተኛ፣ ወይም ጥፋተኛው በሞግዚትነት የሚያሳድገው ልጅ፣ ወይም እንዲጠብቀው ወይም እንዲንከባከበው በአደራ የተሰጠው ልጅ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ በቀጥታ በእርሱ ጥገኝነት ወይም ቁጥጥር ሥር የሚገኝ ልጅ እንደሆነ | 17 |
| 627/3 እና 627/4/ሐ | 4 | በደረጃ 2 የተመለከተው ተበዳይ የጥፋተኛው ተማሪ፣ የሙያ መለማመጃ ትምህርት ተማሪ፣ የቤት ሠራተኛ፣ ወይም ጥፋተኛው በሞግዚትነት የሚያሳድገው ልጅ፣ ወይም እንዲጠብቀው ወይም እንዲንከባከበው በአደራ የተሰጠው ልጅ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ በቀጥታ በእርሱ ጥገኝነት ወይም ቁጥጥር ሥር የሚገኝ ልጅ ከሆነ | 20 |
| 627/3 እና 628/ለ | 5 | ሞትን በማያስከትል የአባላዘር በሽታ መያዙን እያወቀ የግብረ ሥጋ ግንኙነትን በመሰለ ድርጊት ወይም ለንጽህና ክብር ተቃራኒ በሆነ ማናቸውም ሌላ ዓይነት ድርጊት ተበዳይን በበሽታው ያስያዘ እንደሆነ | 24 |
| 627/3 እና 628/ሀ | 6 | የግብረ ሥጋ ግንኙነትን በመሰለ ድርጊት ወይም ለንጽህና ክብር ተቃራኒ በሆነ ማናቸውም ሌላ ዓይነት ድርጊት ምክንያት ተበዳይ ያረገዘች እንደሆነ | 30 |
| 627/3 እና 628/ለ | 7 | በደረጃ 5 እና 6 ስር የተመለከቱት መስፈርቶች ተደራርበው የተገኙ እንደሆነ | 31 |
| 627/3 እና | 8 | ሞትን በሚያስከትል የአባላዘር በሽታ መያዙን እያወቀ ከተበዳይ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነትን የመሰለ ድርጊት | 32 |

www.abyssinialaw.com

| | | | |
|---|---|---|---|
| 628/ሐ | | ወይም ለንጽህና ክብር ተቃራኒ የሆነ ማናቸውንም ሌላ ዓይነት ድርጊት በመፈጸም በበሽታው ያስያዘ እንደሆነ | |
| 627/3 እና 628/ሐ | 9 | በደረጃ 6 እና 8 ስር የተመለከቱት መስፈርቶች ተደራርበው የተገኙ እንደሆነ | 33 |
| 627/3 እና 628/ሐ | 10 | ተበዳይ የግብረ ሥጋ ግንኙነትን በመሰለ ድርጊት ወይም ለንጽህና ክብር ተቃራኒ በሆነ ማናቸውም ሌላ ዓይነት ድርጊት ምክንያት በደረሰበት ከባድ ኀዘን ወይም ጭንቀት፣ ሀፍረት ወይም ተስፋ መቁረጥ የተነሳ ራሱን የገደለ እንደሆነ | 34 |

## በሕጻናት ልጆች ላይ የሚፈጸም የግብረ ሥጋ ድፍረት በደል (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 627/5)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 627/5 | 1 | ዕድሜው አስራ ሦስት ዓመት ካልሞላው ህጻን ልጅ ጋር የተደረገው የግብረ ሥጋ ግንኙነት ወይም የግብረ ሥጋ ግንኙነትን የመሰለ ድርጊት ወይም ለንጽህና ክብር ተቃራኒ የሆነው ማናቸውም ሌላ ዓይነት ድርጊት በተበዳይ ላይ ከባድ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳትን ወይም ሞትን ያስከተለ እንደሆነ | 38 |

www.abyssinialaw.com

# ርዕስ ሰባት

## በንብረት መብቶች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች

### አንቀጽ 16. የስርቆት ወንጀሎች (665 እና 669)

1. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 665 እና 669 ተከሰው ጥፋተኝነታቸው በፍርድ ቤት በሚረጋገጥባቸው ወንጀል አድራጊዎች ላይ ቅጣት የሚወሰነው ከዚህ ቀጥሎ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ነው፡፡

2. የስርቆት ወንጀልን (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 665) በተመለከተ በወንጀሉ የተገኘው ወይም ሊገኝ የታሰበው የገንዘቡ ወይም ንብረቱ ጥቅም ግምትን መሠረት በማድረግ የጥቅሙን መጨመር ታሳቢ ባደረገ መልኩ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ስምንት የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ሁለት የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣

   ሀ. ድንጋጌውን አስመልክቶ የተቀመጠው የመቀጮ ሠንጠረዥ እንደተጠበቀ ሆኖ ፍ/ቤቱ የወንጀል ድርጊት ፈፃሚውን ወንጀል የማድረግ ሀሳብ ክፍል (intention) ለመቅጣት በቂ አይደለም ብሎ ሲያምን ምክንያቱን በመግለፅ ሁለት እርከን በማሳደግ የቅጣቱን መነሻ ሊወስን ይችላል፡፡

   ለ. ወንጀሉ የተፈጸመበት ሰው ወይም ድርጅት በተሰረቀበት ሀብት/ንብረት ምክንያት የእለት ኑሮው ወይም የድርጅቱ ስራ አደጋ ላይ የወደቀ ከሆነ የገንዘብ መጠኑን መሠረት አድርጎ ከተመደበበት የቅጣት እርከን በሁለት እርከን ወደላይ ያሣድጋል፡፡

   ሐ. የተሰረቀው ንብረት ለምሳሌ ፈንጂ፣ ተቀጣጣይ ወዘተ ከሆነ የገንዘብ መጠኑን መሠረት አድርጎ ከተመደበበት የቅጣት እርከን በሁለት እርከን ደረጃ ወደላይ ያሣድጋል፡፡

   መ. በዚህ ድንጋጌ በተራ ቁጥር ‹ሀ› ፣ ‹ለ› እና ‹ሐ› የተመለከቱት ምክንያቶች ተደራርበው በተገኙ ጊዜ፣ እያንዳንዱ የሚያስጨምረው እርከን ተደምሮ

www.abyssinialaw.com

የሚያስገኘው እርከን ድረስ ከፍ ይላል፡፡ ይሁንና በወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል ለወንጀሉ ከተቀመጠው የቅጣት ጣሪያ በላይ አይሄድም፡፡

4. ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 669 (ከባድ ስርቆት) ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 665 የተዘጋጀውን የገንዘብ መጠን መነሻ መሠረት ባደረገ መልኩ እና በድንጋጌው የተመለከቱትን ማክበጃዎች ማለትም ‹የተሰረቀው እቃ ዓይነት›፣ ‹ድርጊቱን የፈጸመው አድራጊ ማንነት›፣ ‹የወንጀል አፈጻጸሙን› መሠረት ባደረገ መልኩ ዘጠኝ የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

5. ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም በወንጀል ሕግ አንቀጽ 669 የተመለከቱት ሦስቱ ማክበጃ ምክንያቶች የቅጣት ማክበጃ የሚል ስያሜ ተሰጥቷቸዋል፡፡

6. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 669 ወንጀሉን የሚያከብዱ ምክንያቶች ከአንድ በላይ ተደራርበው በሚገኙበት ጊዜ የወንጀል ደረጃውና መነሻ ቅጣቱ ከፍ እንዲል ተደርጓል፡፡

7. በወንጀሉ የተገኘውን የጥቅም መጠን መገመት ባልተቻለ ጊዜ ወይም በገንዘብ የሚገመት ካልሆነ ፍ/ቤቱ ምክንያቱን በማስቀመጥ በቅጣት እርከኑ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ባለው ደረጃ እና እርከን መሠረት ሊወስን ይችላል፡፡

## ስርቆት (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 665/1)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 665/1 | 1 | እስከ ብር 100 | 6 |
| 665/1 | 2 | ከብር 101-500 | 8 |
| 665/1 | 3 | ከብር 501.00-1,000.00 | 10 |

www.abyssinialaw.com

| | | | |
|---|---|---|---|
| 665/1 | 4 | ከብር 1,001.00-10,000.00 | 12 |
| 665/1 | 5 | ከብር 10,001.00-100,000.00 | 14 |
| 665/1 | 6 | ከብር 100,001.00-500,000.00 | 16 |
| 665/1 | 7 | ከብር 500,001.00-1,000,000.00 | 18 |
| 665/1 | 8 | ከብር 1,000,000.00 በላይ | 20 |

## ከባድ ስርቆት (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 669)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 669 | 1 | እስከ ብር 1,000.00 ሆኖ በ669 የተመለከተው አንድ ማክበጃ ተሟልቶ ሲገኝ | 10 |
| 669 | 2 | 1. እስከ ብር 1,000.00 ሆኖ ሁለት ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ ወይም<br>2. ከብር 1,001.00 እስከ ብር 2,000.00 ሆኖ አንድ ማክበጃ ተሟልቶ ሲገኝ | 13 |
| 669 | 3 | 1. እስከ ብር 1,000.00 ሆኖ ሶስት ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ ወይም<br>2. ከብር 1,001.00 እስከ ብር 2,000.00 ሆኖ ሁለት ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ | 16 |

www.abyssinialaw.com

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ወይም<br>3. ከብር 2,001.00 እስከ ብር 4,000.00 ሆኖ አንድ ማክበጃ ተሟልቶ ሲገኝ | |
| 669 | 4 | 1. ከብር 1,001.00 እስከ 2,000.00 ሆኖ ሶስቱም ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ፣ ወይም<br>2. ከብር 2,001.00 እስከ 4,000.00 ሆኖ ሁለት ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ ወይም<br>3. ከብር 4,001.00 እስከ 10,000.00 ሆኖ አንድ ማክበጃ ተሟልተው ሲገኙ | 19 |
| 669 | 5 | 1. ከብር 2,001.00 እስከ ብር 4,000.00 ሆኖ ሶስቱም ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ፣ ወይም<br>2. ከብር 4,001.00 እስከ ብር 10,000.00 ሆኖ ሁለቱ ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ ወይም<br>3. ከብር 10,001.00 እስከ 50,000.00 ሆኖ አንድ ማክበጃ ተሟልቶ ሲገኝ | 22 |
| 669 | 6 | 1. ከብር 4,001.00 እስከ 10,000.00 ሆኖ ሶስቱም ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ ወይም<br>2. ከብር 10,001.00 እስከ 50,000.00 ሆኖ ሁለት ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ | 24 |

www.abyssinialaw.com

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ወይም<br>3. ከብር 50,001.00 እስከ 100,000.00 ሆኖ አንድ ማክበጃ ተሟልቶ ሲገኝ | |
| 669 | 7 | 1. ከብር 10,001.00 እስከ 50,000.00 ሆኖ ሶስቱም ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ ወይም<br>2. ከብር 50,001.00 እስከ 100,000.00 ሆኖ ሁለት ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ ወይም<br>3. ከብር 100,000.00 በላይ ሆኖ አንድ ማክበጃ ተሟልቶ ሲገኝ | 26 |
| 669 | 8 | 1. ከብር 50,001.00 እስከ 100,000.00 ሆኖ ሶስቱም ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ ወይም<br>2. ከ100,000.00 በላይ ሆኖ ሁለት ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ | 28 |
| 669 | 9 | ከብር 100,000.00 በላይ ሆኖ ሶስቱም ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ | 30 |

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 17. የውንብድና ወንጀሎች (670 እና 671)

1. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 670 እና 671 ተከሰው ጥፋተኝነታቸው በፍርድ ቤት በሚረጋገጥባቸው ወንጀል አድራጊዎች ላይ ቅጣት የሚወሰነው ከዚህ ቀጥሎ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ነው፡፡

2. የውንብድና ወንጀል እንደ ስርቆትና ማታለል ወንጀል የማይገባ ጥቅምን ለማግኘት የሚፈጸም ወንጀል በመሆኑ በወንጀሉ የተገኘው ወይም ሊገኝ የታሰበው ጥቅም ወይም የደረሰው ወይም ሊደርስ የታሰበው ጉዳትን መጠን መሠረት በማድረግ፣ እንዲሁም የውንብድና ወንጀል ከስርቆት ወንጀል የሚለየው ሀይልን በመጠቀም በመሆኑ፣

   ሀ. የተገኘ ወይም ሊገኝ የታሰበውን የገንዘብ ጥቅም ወይም የደረሰ ወይም ሊደርስ የታሰበውን ጉዳት እና

   ለ. የሀይል አጠቃቀሙን መሠረት ባደረገ መልኩ

   ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 670 ዘጠኝ፣ ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 671(1) ዘጠኝ፣ እንዲሁም ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 671(2) ሁለት የወንጀል ደረጃዎች በአባሪ ሦስት ተዘጋጅተዋል፡፡

3. በዚህ ድንጋጌ ንኡስ አንቀጽ 2 (ለ) እንደተመለከተው የሀይል አጠቃቀምን በተመለከተ ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ ደረጃ የወጣላቸው ሲሆን እነርሱም የማስፈራራቱና ሀይል የመጠቀሙ ተግባር የተፈጸመው፣

   ሀ. መሳሪያ ሳይያዝ በሆነ ጊዜ፣ (ዝቅተኛ)

   ለ. መሳሪያ ተይዞ ከሆነ (መካከለኛ)

   ሐ. የጦር መሳሪያ በመያዝ ከሆነ (ከፍተኛ) በማለት

   እንደቅደም ተከተላቸው የወንጀል አፈጻጸሙን የሚያከብዱ እንደሚሆኑ ታሳቢ በማድረግ የወንጀል ደረጃዎቹ ተዘጋጅተዋል፡፡

www.abyssinialaw.com

4. የወንጀል ሕግ አንቀጽ 671/1 ቅጣቱን ለማክበድ በተቋቋመ የወንበዴ ቡድን አባል መሆንን ያካተተ ስለሆነ፣ በዚህ መሠረት የወንበዴ ቡድን አባል መሆን ቅጣትን የሚያከብድ በሚሆን መልኩ የወንጀል ደረጃዎችን ለማዘጋጀት ሥራ ላይ ውሏል፡፡

**ውንብድና (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 670)**

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 670 | 1 | ጉዳት የሚያደርሱ መሳሪያዎችን ሳይዝ፣ የገጠመውን ተቃውሞ ለማስወገድ ከባድ ዛቻ እና የማንገላታት ተግባር ወይም የሀይል ተግባር የፈጸመ እንደሆነ እና በወንጀሉ የተገኘው የገንዘብ ጥቅም እስከ ብር 2,000.00 የሆነ እንደሆነ | 11 |
| 670 | 2 | 1. ጉዳት የሚያደርሱ መሳሪያዎችን በመያዝ የገጠመውን ተቃውሞ ለማስወገድ ከባድ ዛቻ እና የማንገላታት ተግባር ወይም የሀይል ተግባር የፈጸመ እና በወንጀሉ የተገኘው ጥቅም እስከ ብር 2,000 ከሆነ ወይም<br>2. ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 2,001-10,000 የሆነ እንደሆነ | 13 |
| 670 | 3 | 1. የጦር መሳሪያ በመያዝ የገጠመውን ተቃውሞ ለማስወገድ ከባድ ዛቻ እና የማንገላታት ተግባር ወይም የሀይል ተግባር የፈጸመ እና በወንጀሉ የተገኘ ጥቅም እስከ ብር 2,000 ከሆነ፣ ወይም | 15 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | 2. ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 10,001- 30,000 ከሆነ ወይም<br>3. ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 2,001-10,000.00 ከሆነ፣ | |
| 670 | 4 | 1. ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 30,001.00-100,000.00 ከሆነ ወይም<br>2. ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 10,001.00-30,000.00 ከሆነ ወይም<br>3. ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከብር 2,001.00-10,000.00 ከሆነ፣ | 17 |
| 670 | 5 | 1. ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 10,001.00-30,000.00 ከሆነ ወይም፣<br>2. ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 30,001.00-100,000.00 ከሆነ ወይም<br>3. ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከብር 100,001.00-300,000.00 ከሆነ | 19 |
| 670 | 6 | 1. ድርጊቱ በደረጃ 1 የተፈጸመው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 300,001.00-1,000,000.00 ከሆነ ወይም<br>2. ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 100,001.00-300,000.00 ከሆነ | 21 |

www.abyssinialaw.com

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ወይም<br>3. ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከብር 300,001.00-1,000,000.00 ከሆነ | |
| 670 | 7 | 1. ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 1,000,000.00 በላይ ከሆነ ወይም፣<br>2. ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 300,001-እስከ 1,000,000 ብር ከሆነ ወይም<br>3. ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከብር 100,001.00-300,000.00 ከሆነ | 23 |
| 670 | 8 | 1. ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 1,000,000.00 በላይ ከሆነ ወይም<br>2. ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከብር 300,001.00-1,000,000.00 ከሆነ | 25 |
| 670 | 9 | ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከብር 1,000,000.00 በላይ ከሆነ | 29 |

www.abyssinialaw.com

## ከባድ ውንብድና (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 671/1)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 671/1 | 1 | ጉዳት የሚያደርሱ መሳሪያዎችን ሳይዝ፣ ወንጀሉ በቡድን የተፈጸመ እንደሆነና የገንዘብ መጠኑ እስከ ብር 2,000.00 የሚደርስ እንደሆነ | 21 |
| 671/1 | 2 | 1. ጉዳት የሚያደርሱ መሳሪያዎችን በመያዝ ያስፈራራ፣ ወይም የአካል ጉዳት ያደረሰ እንደሆነና የገንዘቡ መጠን እስከ ብር 2,000.00 የሚደርስ እንደሆነ ወይም<br>2. ድርጊቱ በቡድን የተፈጸመ ሆኖ ያስፈራራ ወይም ዘላቂ ያልሆነ የአካል ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ እና የገንዘብ መጠኑ እስከ ብር 2,000.00 የሚደርስ እንደሆነ ወይም<br>3. ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከብር 2,001.00-10,000.00 የሚደርስ እንደሆነ | 23 |

www.abyssinialaw.com

| | | | |
|---|---|---|---|
| 671/1 | 3 | 1. የጦር መሳሪያ ይዞ ያስፈራራ ወይም የአካል ጉዳት ያደረሰ እንደሆነና የገንዘብ መጠኑም እስከ ብር 2,000.00 የሆነ እንደሆነ ወይም<br>2. ድርጊቱ በቡድን የተፈጸመ ሆኖ ጉዳት የሚያደርሱ መሳሪያዎችን ወይም የጦር መሳሪያ በመያዝ ያስፈራራ ወይም ዘላቂ ያልሆነ ጉዳት ያደረሰ ከሆነና የገንዘብ መጠኑም እስከ ብር 2,000.00 የሆነ እንደሆነ ወይም<br>3. ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 10,001.00-30,000.00 ከሆነ ወይም፣<br>4. ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 2,001.00-10,000.00 ከሆነ | 25 |
| 671/1 | 4 | 1. ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 30,001.00-100,000.00 ከሆነ ወይም<br>2. ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከብር 10,001.00-30,000.00 ከሆነ ወይም<br>3. ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 2,001.00-10,000.00 ከሆነ | 27 |
| 671/1 | 5 | 1. ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 100,00.00-300,000.00 ከሆነ ወይም<br>2. ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከብር 30,001.00-100,000.00 ከሆነ ወይም<br>3. ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 10,001.00-30,000.00 ከሆነ | 29 |

www.abyssinialaw.com

| | | | |
|---|---|---|---|
| 671/1 | 6 | 1. ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 300,001.00-1,000,000.00 ከሆነ ወይም<br>2. ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከብር 100,001.00-300,000.00 ከሆነ ወይም<br>3. ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 30,001.00-100,000.00 ከሆነ | 30 |
| 671/1 | 7 | 1. ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 1,000,001.00 በላይ ከሆነ ወይም<br>2. ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከብር 300,001.00-1,000,000.00 ከሆነ ወይም<br>3. ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 100,001.00-300,000.00 ከሆነ | 32 |
| 671/1 | 8 | 1. ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከብር 100,000.00 በላይ ከሆነ ወይም<br>2. ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 300,001.00-1,000,000.00 ከሆነ | 34 |
| 671/1 | 9 | ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከብር 1,000,000.00 በላይ ከሆነ | 36 |

www.abyssinialaw.com

## ከባድ ውንብድና (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 671/2)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| 671/2 | 1 | ወንጀል ለመፈፀም ከተደራጀ ቡድን ጋር በመሆን ወይም የጦር መሣሪያ ወይም ሌላ አደገኛ መሣሪያ በመያዝ የሕዝብ ፀጥታን አደጋ ላይ የሚጥል ወይም የተለየ ጨካኝነትን የሚያሳይ ዘዴን የተጠቀመ ወይም የተፈፀመው ተግባር ዘላቂ የአካል ጉዳትን ወይም ሞትን ያስከተለ እንደሆነ | 38 | |
| 671/2 | 2 | በጦር መሣሪያ አማካይነት በልማደኛነት በቡድን በሚፈፀም ውንብድና የተለየ ጨካኝነትን የሚያሳይ ዘዴ በመጠቀም የተፈፀመው ተግባር ሞትን ያስከተለ እንደሆነ | 39 | |

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 18. የማታለል ወንጀሎች (692 እና 693)

1. በዚህ መመሪያ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 692 እና 693 ተከሰው ጥፋተኝነታቸው በፍርድ ቤት በሚረጋገጠባቸው ወንጀል አድራጊዎች ላይ ቅጣት የሚወሰነው ከዚህ ቀጥሎ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ነው፡፡
2. የማታለል ወንጀል (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 692) በተመለከተ በወንጀሉ የተገኘው ወይም ሊገኝ የታሰበው የገንዘቡ ወይም ንብረቱ ጥቅም ግምትን መሠረት በማድረግ የጥቅሙን መጨመር ታሳቢ ባደረገ መልኩ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ስምንት የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ሁለት የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣

   ሀ. ድንጋጌውን አስመልክቶ የተቀመጠው የመቀጮ ሠንጠረዥ እንደተጠበቀ ሆኖ ፍ/ቤቱ የወንጀል ድርጊት ፈፃሚውን ወንጀል የማድረግ ሀሳብ ክፍል (intention) ለመቅጣት በቂ አይደለም ብሎ ሲያምን ምክንያቱን በመግለፅ ሁለት እርከን በማሳደግ የቅጣቱን መነሻ ሊወስን ይችላል፡፡

   ለ. ወንጀሉ የተፈጸመበት ሰው ወይም ድርጅት በማታለሉ ተግባር በተወሰደበት ገንዘብ ወይም ንብረት ምክንያት የእለት ኑሮው ወይም የድርጅቱ ስራ አደጋ ላይ የወደቀ ከሆነ የገንዘብ መጠኑን መሠረት አድርጎ ከተመደበበት የቅጣት እርከን በሁለት እርከን ወደላይ ያድጋል፡፡

   ሐ. የተወሰደው ንብረት ለምሳሌ ፈንጂ፣ ተቀጣጣይ ወዘተ ከሆነ የገንዘብ መጠኑን መሠረት አድርጎ ከተመደበበት የቅጣት እርከን በሁለት እርከን ወደ ላይ ያድጋል፡፡

   መ. የተወሰደው ንብረት ለወንጀል ተጎጂው ልዩ ትርጉም ያለው ከሆነና ወንጀል አድራጊውም ይህንን እያወቀ የወሰደው ከሆነ በአንድ እርከን ወደ ላይ ያድጋል፡፡

   ሠ. በዚህ ድንጋጌ በ‹ሀ›፣ ‹ለ›፣ ‹ሐ› እና ‹መ› የተመለከቱት ምክንያቶች ተደራርበው በተገኙ ጊዜ፣ እያንዳንዱ የሚያስጨምረው እርከን ተደምሮ የሚያስገኘው እርከን ድረስ ከፍ ይላል፡፡ ይሁንና በወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል ለወንጀሉ ከተቀመጠው የቅጣት ጣሪያ በላይ አይሄድም፡፡

www.abyssinialaw.com

4. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 693 ‹የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ማውጣት› ወንጀል በተመለከተ የገንዘቡን መጠን መሠረት በማድረግ የጥቅሙን መጨመር ታሳቢ ባደረገ መልኩ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ አሥራ አንድ የወንጀል ደረጃዎች በአባሪ ሶስት ተዘጋጅተዋል፡፡

## አታላይነት (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 692/1)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| 692/1 | 1 | እስከ ብር 100.00 | 6 | 1 |
| 692/1 | 2 | ከብር 101.00-500.00 | 8 | 1 |
| 692/1 | 3 | ከብር 501.00-1,000.00 | 10 | 1 |
| 692/1 | 4 | ከብር 1,001.00-10,000.00 | 12 | 2 |
| 692/1 | 5 | ከብር 10,001.00-100,000.00 | 14 | 3 |
| 692/1 | 6 | ከብር 100,001.00-500,000.00 | 16 | 4 |
| 692/1 | 7 | ከብር 500,001.00-1000,000.00 | 18 | 5 |
| 692/1 | 8 | ከብር 1000,000.00 በላይ | 20 | 6 |

www.abyssinialaw.com

## የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ማውጣት (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 693/1)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| 693/1 | 1 | እስከ ብር 5000.00 | 5 | - |
| 693/1 | 2 | ከብር 5001.00-10,000.00 | 7 | - |
| 693/1 | 3 | ከብር 10,001.00-25,000.00 | 9 | 1 |
| 693/1 | 4 | ከብር 25,001.00-50,000.00 | 11 | 2 |
| 693/1 | 5 | ከብር 50,001.00-100,000.00 | 13 | 3 |
| 693/1 | 6 | ከብር 100,001.00-250,000.00 | 15 | 4 |
| 693/1 | 7 | ከብር 250,001.00- 500,000.00 | 17 | 5 |
| 693/1 | 8 | ከብር 500,001.00-1,000,000.00 | 19 | 6 |
| 693/1 | 9 | ከብር 1,000,001.00-2000,000.00 | 21 | 6 |
| 693/1 | 10 | ከብር 2,000,001.00-5000,000.00 | 23 | 6 |
| 693/1 | 11 | ከብር 5,000,000.00 በላይ | 25 | 6 |

www.abyssinialaw.com

በቸልተኝነት የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ማውጣት (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 693/2)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| 693/2 | 1 | ድርጊቱ የተፈጸመው በቸልተኝነት ከሆነ | 4 | 4 |

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## ደረጃ ላልወጣላቸው ወንጀሎች በቅጣት ማንዋሉ መሠረት ስለሚሰራበት ሁኔታ

### አንቀጽ 19. ደረጃ ያልወጣላቸው ወንጀሎች የወንጀል ደረጃና የቅጣት መነሻ እርከን አወሳሰን

1. ወደፊት በወንጀል ሕጉ እና በሌሎች የወንጀል ሕጎች ለተደነገጉት ዝርዝር የወንጀል ድርጊቶች የወንጀል ደረጃዎች እየተለየ የሚወጣላቸው ሆኖ፣ ደረጃ ወጥቶ እስከሚመደብ ድረስ ፍርድ ቤቱ ከዚህ በታች በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ቅጣት ይወስናል፡፡
2. ወንጀሉን የሚደነግገው ድንጋጌ በቀላል እስራት ወይም በጽኑ እስራት ሊያስቀጣ እንደሚችል በደነገገ ጊዜ ፍርድ ቤቱ ደረጃውን ለማውጣት በቅድሚያ በቀላል እስራት ወይም በጽኑ እስራት እንደሚያስቀጣ ይወስናል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ሁለት በተመለከተው መሠረት ከተወሰነ በኋላ፣ ፍርድ ቤቱ በወንጀል ድንጋጌው ከተቀመጠው መስፈርት (ፍሬነገር) አንጻር እና የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶችን ታሳቢ ከማድረጉ በፊት ወንጀሉን በክብደቱና በአፈጻጸሙ፣

   ሀ. ቀላል፣

www.abyssinialaw.com

ለ. መካከለኛ፣

ሐ. ከባድ የወንጀል ደረጃ በማለት ይመድባል፡፡

4. ፍርድ ቤቱ ወንጀሉን ‹ቀላል› ‹መካከለኛ› ወይም ‹ከባድ› በማለት ለመመደብ ምክንያቱን በውሳኔ ሰነዱ ላይ ያስቀምጣል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ወይም 3 መሠረት የወንጀሉን ደረጃ ለመወሰን የሚከተሉት እንደመለኪያ ተደርገው ሊወሰዱ ይችላሉ፡፡ ይሁንና ጠቅላላ የቅጣት ማቅለያና ማክበጃ ምክንያቶች ደረጃውን ለመወሠን እንደመለኪያ (መስፈርት) ሊወሠዱ አይችሉም፡፡

ሀ. የወንጀሉ አፈጻጸም ሁኔታ

ለ. የደረሰው ጉዳት ዓይነትና መጠን፣

ሐ. የተገኘው ጥቅም መጠን፣

መ. ወንጀሉ ታስቦ የተሰራ መሆን አለመሆኑ፣

ሠ. ወንጀሉ በቸልተኝነት ሲሰራ የሚያስቀጣ ከሆነ ቸልተኝነቱ የታወቀ ወይም ያልታወቀ ቸልተኝነት መሆኑ፣

6. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 5 በተመለከተው መስፈርት ብቻ ሳይወሰን ፍርድ ቤቱ ደረጃውን ለመወሰን ሌሎች መስፈርቶችን ለመጠቀም ይችላል፡፡

7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 በተመለከተው መሠረት የወንጀል ደረጃው ከተለየ በኋላ ለወንጀል ደረጃው የቅጣት እርከኑን ለመወሰን እንዲቻል በልዩ ክፍሉ ለወንጀሉ በተቀመጠው የቅጣት መነሻና መድረሻ መካከል ያለውን ርዝመት ለአራት እኩል በመክፈል፣

ሀ. በወንጀል ሕግ ለቅጣቱ መነሻ ተብሎ ከተቀመጠው የቅጣት መጠን የሚጀምረው አንድ አራተኛ (ጊዜ ወይም መጠን) እርከን አንድ ይባላል፡፡

ለ. ከመጀመሪያው አንድ አራተኛ ቀጥሎ ያሉት እርከኖች እንደ ቅደም ተከተላቸው እርከን ሁለት፣ እርከን ሶስት፣ እርከን አራት ይባላሉ፡፡

8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ‹ቀላል› በሚለው የወንጀል ደረጃ ውስጥ ለተመደበው ፍርድ ቤቱ በእርከን አንድ ባለው ፍቅድ ሥልጣን (range) ውስጥ መነሻ ቅጣቱን ይወስናል፡፡

www.abyssinialaw.com

9. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 3 መሠረት ‹መካከለኛ› በሚለው የወንጀል ደረጃ ውስጥ ለተመደበው ፍርድ ቤቱ በእርከን ሁለት ባለው ፍቅድ ስልጣን (range) ውስጥ መነሻ ቅጣቱን ይወስናል፡፡

10. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ‹ከባድ› በሚለው የወንጀል ደረጃ ውስጥ ለተመደበው ፍርድ ቤቱ በእርከን ሦስት ባለው ፍቅድ ሥልጣን (range) ውስጥ መነሻ ቅጣቱን ይወስናል፡፡ ሆኖም የተፈፀመው የወንጀል ድርጊት እጅግ ከባድ ነው ብሎ ፍ/ቤቱ ከወሠነ በዚህ ድንጋጌ ሳይወሰን መነሻ ቅጣቱን በእርከን 4 ሥር ሊወስን ይችላል፡፡

11. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 8፣ 9 ወይም 10 መሠረት በፍርድ ቤቱ የተወሰነው መነሻ ቅጣት በአባሪ አንድ በተያያዘው የቅጣት ሠንጠረዥ እርከን የትኛው እርከን ላይ እንደሚወድቅ በመለየት የቅጣት እርከኑን በሰንጠረዡ መሠረት ይለያል፡፡ ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 8፣ 9 ወይም 10 መሠረት ያስቀመጠው የቅጣት መጠን በአባሪ አንድ በተያያዘው የቅጣት ሠንጠረዥ ሁለት ተከታታይ እርከኖች ውስጥ የሚወድቅ ከሆነ፣ በዝቅተኛው እርከን ውስጥ እንዲመደብ ይደረጋል፡፡

12. በዚህ አንቀጽ መሠረት ቅጣታቸው የሚወሰን የወንጀል አይነቶች በመቀጮ ብቻ የሚያስቀጡ ወይም በመቀጮ ወይም በእስር የሚያስቀጡ ወይም በመቀጮ እና በእስር የሚያስቀጡ መሆኑ በተደነገገ ጊዜ፣ ወይም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 92/2 መሠረት መቀጮ መጣል የሚያስፈልግ በሆነ ጊዜ ፍርድ ቤቱ በወንጀል ሕጉ ጠቅላላ ወይም ልዩ ክፍል ወይም በሌላ ሕግ የተቀመጠውን ጣሪያ መሠረት በማድረግ፣ ‹ለከባዱ› በሕጉ እስከተመለከተው ጣሪያ ድረስ፣ ‹መካከለኛ› ለሆነው በሕጉ ከተመለከተው ጣሪያ አንድ ሶስተኛ በመቀነስ የሚደረስበትን መጠን ጣሪያ በማድረግ፣ እንዲሁም ‹ቀላል› ለሆነው ከጣሪያው በሁለት ሦስተኛ ዝቅ ብሎ በሚደርስበት ጣሪያ ሳይበልጥ መቀጮውን ይወስናል፡፡

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 20. ቅጣቱ በወንጀል ሕግ ተለይቶ በሚታወቅበት ጊዜ ስለ ቅጣት አጣጣል

1. በወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል ወይም በልዩ ልዩ ሕጎች ለተፈጸመው ወንጀል የሚጣለው ቅጣት ለፍርድ ቤት ፍቅድ ሥልጣን ያልሰጠ አንድ የታወቀ ቅጣት ከሆነ ይህ ቅጣት መነሻ ቅጣት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡
2. በወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል ወይም በልዩ ልዩ ሕጎች ለተፈጸመው ወንጀል የሚጣለው ቅጣት ከሁለት ያልበለጡ አማራጮች ያሉት ከሆነ በዚህ መመሪያ መመራት ሳያስፈልግ ጥፋቱ ከባድ ወይም ቀላል መሆኑ ይለያል፣ ቀላል ከሆነ ዝቅተኛው አማራጭ ወይም ከባድ ከሆነ ከፍተኛው አማራጭ መነሻ ቅጣት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

www.abyssinialaw.com

# ክፍል አራት

# የቅጣት ማክበጃና ማቅለያዎችን ስለ ማስላት

## ንዑስ ክፍል አንድ

## የቅጣት ማክበጃዎችን ስለ ማስላት

### አንቀጽ 21. ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች በሚኖሩበት ጊዜ ቅጣቱ ስለሚከብድበት አሰራር

ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች በሚኖሩ ጊዜ ቅጣቱ የሚከብደው ከዚህ ቀጥሎ በተመለከተው መሠረት ይሆናል፡፡

1. ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም በወንጀል ሕግ አንቀጽ 84 ንዑስ አንቀጽ 1 ከ‹ሀ› እስከ ‹ሠ› በአምስት ንዑሳን ድንጋጌዎች ተዘርዝረው የተመለከቱት ማክበጃ ምክንያቶች እያንዳንዳቸው እንደ አንድ ማክበጃ ምክንያት በጠቅላላው እንደ አምስት የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች ተደርገው ተወስደዋል፡፡ ሆኖም በአንዱ ፊደል ስር የተደራረቡ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች በተገኙ ጊዜ ፍ/ቤቱ ምክንያቱን በመግለፅ ቅጣቱን እንደ ሁኔታው በማክበድ ሊወስን ይችላል፡፡ ነገር ግን በተደራራቢነት የሚወሰዱ እና በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ፊደላት ሥር የሚገኙ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች አጠቃላይ ብዛት ከአምስት መብለጥ የለባቸውም፡፡

2. በእያንዳንዱ ድንጋጌ ‹ሀ›፣‹ለ›፣‹ሐ›፣‹መ›፣‹ሠ› ከተመለከቱት ምክንያቶች አንዱ እንኳን ተሟልቶ ቢገኝ አንድ የቅጣት ማክበጃ እንደተሟላ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

3. በእያንዳንዱ ድንጋጌ ‹ሀ›፣‹ለ›፣‹ሐ›፣‹መ›፣‹ሠ› ከተመለከቱት ምክንያቶች አንዱ ወይም በከፊል ወይም በሙሉ ተሟልተው ሲገኙ፣ ፍርድ ቤቱ ቅጣቱ ሲከብድ የሚደርስበት የቅጣት እርከን ውስጥ ባለው ፍቅድ ስልጣን (range) ከዝቅተኛው እስከ ጣሪያው ባለው ውስጥ ቅጣቱ የሚወድቅበትን ይወስናል፡፡

4. ፍርድ ቤቱ ለእያንዳንዱ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት መነሻ ቅጣቱ ከሚያርፍበት የቅጣት እርከን አንድ እርከን ወደላይ ይጨምራል፡፡ ስለሆነም በቅጣት ማክበጃዎቹ ቁጥር ልክ የቅጣት እርከኑም እንደዚሁ ያድጋል፡፡ ይሁንና በወንጀል ሕጉ ልዩ

www.abyssinialaw.com

ክፍል ወይም በሌሎች ልዩ ልዩ የወንጀል ሕጎች ለወንጀሉ ከተቀመጠው የቅጣት ጣሪያ ማለፍ አይችልም፡፡

## አንቀጽ 22. ልዩ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች በሚኖሩ ጊዜ ቅጣቱ ስለሚከብድበት አሰራር

1. ወንጀል አድራጊው በተደራራቢ ወንጀሎች ጥፋተኛ መሆኑ የተረጋገጠ በሆነ ጊዜ፣

   ሀ. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 184 በተመለከተው መሠረት ለእያንዳንዱ ወንጀል ቅጣት ወስኖ የሚደመር በሆነ ጊዜ በዚህ መመሪያ መሠረት ለእያንዳንዱ ወንጀል መነሻ ቅጣት ካስቀመጠ በኋላ እነዚህን በመደመር ድምሩ የቅጣት መጠን የሚያርፍበትን ዝቅተኛ የቅጣት እርከን በመምረጥ እርከኑን ይለያል፡፡ በመቀጠልም በወንጀል ሕግ ከተመለከተው ጣሪያ ሳይበልጥ ጠቅላላ ማክበጃ ምክንያቶችን መሠረት በማድረግ ቅጣቱ ያድጋል፡፡

   ለ. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 187 ንዑስ አንቀጽ 1 ሁለተኛ ፓራግራፍ እና ንዑስ አንቀጽ 2/ለ እንደተመለከተው ቅጣቱ የሚከብድ በሆነ ጊዜ ለእያንዳንዱ ተደራራቢ ወንጀል ከመነሻው እርከን በሁለት እርከን እንዲያድግ ይደርጋል፡፡ በመቀጠልም ጠቅላላ ቅጣት ማክበጃ ምክንያቶችን መሠረት አድርጎ ይከብዳል፡፡ ይሁንና ለከባዱ ወንጀል ከተደነገገው ጣሪያ መብለጥ የለበትም፡፡

2. ጥፋተኛው ደጋጋሚ ወንጀለኛ በሆነ ጊዜ ፍርድ ቤቱ ለአዲሱ ወንጀል የመነሻ ቅጣቱ የሚያርፍበትን እርከን በዚህ መመሪያ መሠረት ከለየ በኋላ ቅጣቱን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 188 በተመለከተው መሠረት ከአንድ እርከን ጀምሮ ቅጣቱን ሊያሳድግ ይችላል፡፡ በመቀጠልም ጠቅላላ ቅጣት ማክበጃ ምክንያቶችን መሠረት በማድረግ ቅጣቱን ያከብዳል፡፡ ነገር ግን በወንጀል ሕጉ ጠቅላላ ክፍል ለቅጣቱ ዓይነት ከተቀመጠው ጣሪያ ሊበልጥ አይችልም፡፡

www.abyssinialaw.com

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## የቅጣት ማቅለያዎችን ስለ ማስላት

### አንቀጽ 23. ጠቅላላ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች በሚኖሩበት ጊዜ ስለሚኖረው አሰራር

ጠቅላላ የቅጣት ማቅለያዎች በሚኖሩ ጊዜ ቅጣቱ የሚቀለው ከዚህ ቀጥሎ በተመለከተው መሠረት ይሆናል፡፡

1. ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም በወንጀል ሕግ አንቀጽ 82 ንዑስ አንቀጽ 1 ከ‹ሀ› እስከ ‹ሠ› በአምስት ንዑሳን ድንጋጌዎች ተዘርዝረው የተመለከቱት ማቅለያ ምክንያቶች እያንዳንዳቸው እንደ አንድ ማቅለያ ምክንያት በጠቅላላው እንደ አምስት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ተደርገው ተወስደዋል፡፡ ሆኖም በአንዱ ፊደል ስር የተደራረቡ የቅጣት ማቅለያ ድንጋጌዎች በተገኙ ጊዜ ፍ/ቤቱ ምክንያቱን በመግለጽ ቅጣቱን እንደ ሁኔታው በማቅለል ሊወስን ይችላል፡፡ ነገር ግን በተደራራቢነት የሚወሰዱ እና በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ፊደላት ሥር የሚገኙ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች አጠቃላይ ብዛት ከአምስት መብለጥ የለባቸውም፡፡
2. በእያንዳንዱ ድንጋጌ ‹ሀ›፣‹ለ›፣‹ሐ›፣‹መ›፣‹ሠ› ከተመለከቱት ምክንያቶች አንዱ እንኳን ተሟልቶ ቢገኝ አንድ የቅጣት ማቅለያ እንደተሟላ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡
3. በእያንዳንዱ ድንጋጌ ‹ሀ›፣‹ለ›፣‹ሐ›፣‹መ›፣‹ሠ› ከተመለከቱት ምክንያቶች አንዱ ወይም በከፊል ወይም በሙሉ ተሟልተው ሲገኙ፣ ፍርድ ቤቱ ቅጣቱ ሲቀል የሚደርስበት የቅጣት እርከን ውስጥ ባለው ፍቅድ ስልጣን (range) ከዝቅተኛው እስከ ጣሪያው ባለው ውስጥ ቅጣቱ የሚወድቅበትን ይወስናል፡፡
4. በቀላል እና በፅኑ እስራት ለሚያስቀጡ ወንጀሎች ፍርድ ቤቱ ለእያንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት መነሻ ቅጣቱ ከሚያርፍበት የቅጣት እርከን አንድ እርከን ወደታች ይቀንሳል፡፡ ስለሆነም በቅጣት ማቅለያዎቹ ቁጥር ልክ የቅጣት እርከኑም እንደዚሁ ይቀንሳል፡፡ ይሁንና በወንጀል ሕግ አንቀጽ 179 ከተደነገገው ዝቅተኛ ወለል በታች ሊወርድ አይችልም፡፡

www.abyssinialaw.com

5. በቀላል እና ፅኑ እስራት የሚያስቀጡ ወንጀሎች ተደራራቢ ሆነው የሚደመሩ በሆነ ጊዜ በቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች የሚቀንሰውን እርከን መጠን ለመወሠን የቀላል እስራት ቅጣት በሕጉ አግባብ ወደ ፅኑ እስራት ተቀይሮ ቅጣቶቹ ተደምረው የሚመጣው ውጤት የቅጣት መነሻ ተደርጎ ይወሠዳል፡፡

## አንቀጽ 24. ልዩ የቅጣት ማቅለያዎች

በወንጀል ሕግ ቅጣትን በመሰለው እንዲያቀል በፈቀደ ጊዜ ፍርድ ቤቱ በዚህ መመሪያ በተመለከተው መሰረት ሳይወሰን ቅጣቱን በማቅለል ይወስናል፡፡

## አንቀጽ 25. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 86 መሠረት የቅጣት ማክበጃና ማቅለያዎች በሚኖሩ ጊዜ ስለሚሰላበት ሁኔታ

ፍርድ ቤቱ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 86 መሠረት የቅጣቱን ማቅለያ ወይም ማክበጃ ምክንያቶች የሚጠቀም በሆነ ጊዜ በዚህ መመሪያ ጠቅላላ ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶች በሚኖሩ ጊዜ እንደሚኖረው አሰራር ቅጣቱን በማክበድ ወይም በማቅለል ይወስናል፡፡

# ክፍል አምስት

# የቅጣት አሰላል ሥነ ሥርዓት

## አንቀጽ 26. የቅጣት አሰላል ሥነ ሥርዓት ቅደም ተከተል

በዚህ መመሪያ መሠረት ፍርድ ቤቱ ቅጣት ሲወስን የሚከተለውን ቅደም ተከተል መሠረት በማድረግ ይሆናል፡፡

1. የወንጀል ደረጃ የወጣላቸውን የወንጀል አይነቶች በተመለከተ፣
   ሀ. የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በዚህ መመሪያ በክፍል ሦስት በተመለከተው መሠረት የወንጀሉን ደረጃ ይወስናል፡፡
   ለ. የወንጀሉ ደረጃ የሚወድቅበትን የቅጣት እርከን በአባሪ አንድ ከተያያዘው የቅጣት ሠንጠረዥ ላይ ይለያል፡፡
   ሐ. ድንጋጌው ቀላልና ፅኑ እስራትን በአማራጭነት ባስቀመጠ ጊዜ ፍ/ቤቱ ወንጀሉ በቀላል እስራት ወይም በጽኑ እስራት የሚያስቀጣ መሆኑን ይወስናል፡፡

www.abyssinialaw.com

መ. በእርከኑ በተቀመጠው የቅጣት መነሻና መድረሻ መካከል ባለው ፍቅድ ስልጣን (range) ውስጥ መነሻ ቅጣት ይወስናል፡፡ ይሁንና ፍርድ ቤቱ የተቀበላቸው የቅጣት ማክበጃ ወይም ማቅለያ ምክንያቶች ካሉ በዚህ ድንጋጌ መሰረት መነሻ ቅጣቱን መወሰን ሳያስፈልግ ቅጣቱን ያከበዳል ወይም ያቀላል፡፡

ሠ. ልዩ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች ካሉ በዚህ መመሪያ መሰረት ቅጣቱን አክብዶ ቅጣቱ የሚደርስበትን እርከን ይወስናል፡፡

ረ. ፍ/ቤቱ በተቀበላቸው ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች መሠረት እርከኑን ይወስናል፡፡ ሆኖም ክርክር የተነሳባቸው የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶችን በማስረጃ ማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በቂ ጊዜ ሰጥቶ ሊያጣራ ይችላል፡፡

ሰ. ፍ/ቤቱ በተቀበላቸው ጠቅላላ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች መሠረት የሚቀንሰውን እርከን በመለየት ቅጣቱን ይወስናል፡፡ ሆኖም ክርክር የተነሳባቸው የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችን በማስረጃ ማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በቂ ጊዜ ሰጥቶ ሊያጣራ ይችላል፡፡

ሸ. የሚጣለው የእስራት ቅጣት ከስድስት ወር ያልበለጠ በሚሆንበት ጊዜ በዚህ መመሪያ ተያይዞ በሚገኘው የቅጣት እርከን ሠንጠረዥ መሠረት በግዴታ ስራ እንዲለወጥ ሊወስን ይችላል፡፡

ቀ. በቅጣት ማቅለያ ጊዜ የእስራት ቅጣትን ወደ መቀጮ መቀየር እንደሚቻል በሕግ በተደነገገው መሠረት ወደ መቀጮ ሲቀየርም በዚህ መመሪያ መሠረት ይሆናል፡፡

2. የወንጀል ደረጃ ያልወጣላቸውን የወንጀል አይነቶች በተመለከተ፡-

ሀ. የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በድንጋጌው በቀላል እስራት ወይም በጽኑ እስራት ሊያስቀጣ እንደሚችል የተደነገገ ከሆነ፣ ፍርድ ቤቱ በቀላል እስራት ወይም በጽኑ እስራት የሚያስቀጣ መሆኑን በቅድሚያ ይለያል፡፡

ለ. የወንጀሉ ከባድነትን በተመለከተ ‹ቀላል› ወይም ‹መካከለኛ› ወይም ‹ከባድ› በማለት ይለያል፡፡

ሐ. በዚህ መመሪያ በተመለከተው መሠረት መነሻ ቅጣቱን በመወሰን፣ በቅጣት እርከን ሠንጠረዥ የሚያርፍበትን የቅጣት እርከን ወይም የመቀጮ እርከን ይለያል፡፡

www.abyssinialaw.com

መ. ከዚህ በመቀጠል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከንዑስ አንቀጽ (ሠ-ቀ) በተመለከተው መሠረት ስሌቱን በመስራት ቅጣቱን ይወስናል፡፡

3. የወንጀል ደረጃ የወጣላቸው እና ያልወጣላቸው የወንጀል ዓይነቶች ተደራረበው ባጋጠሙ ጊዜ ለእያንዳንዱ ወንጀል በዚህ መመሪያ መሠረት የመነሻ ቅጣት ከተወሰነ በኋላ የሁለቱ ድምር የመነሻ ቅጣት ሆኖ ይወሰዳል፡፡

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 27. ከዚህ መመሪያ ውጪ ቅጣት ሊወሰን የሚችልበት ሥርዓት

1. ፍርድ ቤቱ የወንጀል አፈጻጸሙም ሆነ ባህርይው በዚህ መመሪያ ደረጃ በወጣላቸው ሊወከል የማይችል ሆኖ ባገኘው ጊዜ ወይም በዚህ መመሪያ በተቀመጠው መሰረት ቅጣቱን መወሰን የወንጀል ህጉን የቅጣት አላማ እና ግብ የማያሳካ ነው ብሎ ካመነ፣ የዚህን የቅጣት መመሪያ ተግባራዊ ለማድረግ የማይችልበትን ምክንያት በዝርዝር በማስቀመጥ በዚህ መመሪያ ከተቀመጠው በተለየ መልኩ ቅጣት ሊወስን ይችላል፡፡

2. ዳኞች ከመመሪያው ውጪ ቅጣትን ከወሠኑ ዉሳኔዉ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት እንዲተላለፍ ግልፅ ትዕዛዝ ሊሰጡ ይገባል፡፡ የክልል ፍ/ቤቶችን በተመለከተ የውሳኔ ግልባጭ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በኩል ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት እንዲላክ ማድረግ አለባቸው፡፡

3. ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 በተደነገገው መሰረት መመሪያው ከሚያስቀምጠው በተለየ እርከን ላይ እንዲያርፍ በማድረግ የተሰጠውን ውሳኔ ግልባጭ ውሳኔ ከተሰጠበት ጀምሮ በ60 (በስልሳ) ቀናት ውስጥ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ማስተላለፍ ይኖርበታል፡፡

### አንቀጽ 28. የንብረት ግምት መወሰንን በተመለከተ

1. ወንጀሉ የተፈጸመው በውጭ ሀገር መገበያያ ገንዘብ ላይ ከሆነ፣ የገንዘቡ ምንዛሪ መጠን ወንጀሉ ሲፈፀም በነበረው የምንዛሬ ተመን መሠረት ይሆናል፡፡

www.abyssinialaw.com

2. በወንጀሉ የተወሰደው ንብረት በሚሆንበት ጊዜ የንብረቱን ግምት በተመለከተ ተከሳሹ ክርክር ካቀረበ እና የተከሳሹ ክርክር ተቀባይነት ቢያገኝ የቅጣት እርከኑን የሚቀየር ከሆነ እና በፍርድ ቤቱ እምነት በአቃቤ ህግ የቀረበው ግምት ምክንያታዊ ያልሆነ ነው ብሎ ሲያምን የራሱን ግምት በማስቀመጥ ወይም በባለሙያ በማስገመት የወንጀል ደረጃውንና የቅጣት እርከኑን ይወስናል፡፡

3. ከላይ በንዑስ አንቀጽ ሁለት የተመለከተው ቢኖርም ተከራካሪ ወገኖች በግምቱ ላይ ክርክር ባያነሱም ፍ/ቤቱ የንብረቱን ግምት ተገቢ ነው ባለው መንገድ ሊያጣራ ይችላል፡፡

4. ከንብረቱ ልዩ ባህሪ የተነሳ ግምቱን በገንዘብ መተመን ያልተቻለ እንደሆነ ፍ/ቤቱ በራሱ ተገቢ ነው ባለው መንገድ ቅጣቱን ሊወስን ይችላል፡፡

## አንቀጽ 29. ስለቅጣት አስተያየት አቀራረብ

1. አቃቤ ሕጎችም ሆኑ ጥፋተኞች ወይም ጠበቆቻቸው የቅጣት ውሳኔ አስተያየት በሚያቀርቡበት ጊዜ በዚህ መመሪያ መሰረት መሆን አለበት፡፡ ፍ/ቤቶችም በመመሪያው መሠረት የቅጣት አስተያየቶች መቅረባቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

2. በጠበቃ ለማይወከሉ ተከሳሾች በመመሪያው መሰረት የቅጣት አስተያየት ማቅረብ እንዳለባቸው ፍ/ቤቱ ሊገልጽላቸው ይችላል፡፡

## አንቀጽ 30. የተሻረ መመሪያ

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

## አንቀጽ 31. መመሪያው ሥራ ላይ የሚውልበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከጥቅምት 1 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ ሥራ ላይ ይውላል፡፡

ተገኔ ጌታነህ ክፍሌ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ፕሬዚዳንት

www.abyssinialaw.com

## አባሪ አንድ

## ነጻነትን እና ሕይወትን የሚያሳጡ የቅጣት እርከኖች ሰንጠረዥ

| | | |
|---|---|---|
| እርከን 1 | ከ1 ቀን-3 ወር የግዴታ ስራ | ከ1 ብር- 500.00 |
| እርከን 2 | ከ10 ቀን-6 ወር እስራት ወይም<br>ከ10 ቀን-6 ወር የግዴታ ስራ | እስከ ብር - 1000.00 |
| እርከን 3 | ከ2 ወር- 8 ወር እስራት ወይም<br>ከ2 ወር-6 ወር የግዴታ ስራ | እስከ ብር- 1300.00 |
| እርከን 4 | ከ4 ወር- 10 ወር እስራት | እስከ ብር 1600.00 |
| እርከን 5 | ከ6 ወር- 1 አመት እስራት | እስከ ብር 2,000.00 |
| እርከን 6 | ከ8 ወር- 1 አመት ከ2 ወር እስራት | |
| እርከን 7 | ከ1 አመት- 1 አመት ከ6 ወር እስራት | |
| እርከን 8 | ከ1 አመት ከ2 ወር- 1 አመት ከ8 ወር እስራት | |
| እርከን 9 | ከ1 አመት ከ4 ወር- 1 አመት ከ10 ወር እስራት | |
| እርከን 10 | ከ1 አመት ከ6 ወር- 2 አመት እስራት | |
| እርከን 11 | ከ1 አመት ከ8 ወር- 2 አመት ከ2 ወር | |

www.abyssinialaw.com

| | | |
|---|---|---|
| እርከን 12 | ከ2 አመት - 2 አመት ከ6 ወር | |
| እርከን 13 | ከ2 አመት ከ3 ወር-2 አመት ከ9 ወር | |
| እርከን 14 | ከ2 አመት ከ6 ወር-3 አመት | |
| እርከን 15 | ከ2 አመት ከ9 ወር-3 አመት ከ3 ወር | |
| እርከን 16 | ከ3 አመት - 3 አመት ከ7 ወር | ከዚህ ጀምሮ ሬንጁ በ20 በመቶ እያደገ እንዲሄድ ተደርጓል፡ |
| እርከን 17 | ከ3 አመት ከ3 ወር-3 አመት ከ11 ወር | |
| እርከን 18 | ከ3 አመት ከ7 ወር- 4 አመት ከ4 ወር | |
| እርከን 19 | ከ4 አመት- ከ4 ዓመት ከ10 ወር | |
| እርከን 20 | ከ4 አመት ከ5 ወር-5 አመት ከ4 ወር | |
| እርከን 21 | ከ5 አመት - 6 አመት | |
| እርከን 22 | ከ5 አመት ከ6 ወር-6 አመት ከ7 ወር | |
| እርከን 23 | ከ6 አመት- 7 አመት ከ2 ወር | |
| እርከን 24 | ከ6 አመት ከ6 ወር- 7 አመት ከ8 ወር | |
| እርከን 25 | ከ7 አመት- 8 አመት ከ4 ወር | |
| እርከን 26 | ከ7 አመት ከ8 ወር- 9 አመት ከ2 ወር | |

| | | |
|---|---|---|
| እርከን 27 | ከ8 አመት ከ5 ወር- 10 አመት | |
| እርከን 28 | ከ9 አመት - 10 አመት ከ10 ወር | |
| እርከን 29 | ከ10 አመት- 12 አመት | |
| እርከን 30 | ከ11 አመት- 13 አመት ከ2 ወር | |
| እርከን 31 | ከ12 አመት- 14 አመት ከ5 ወር | |
| እርከን 32 | ከ13 አመት- 15 አመት ከ8 ወር | |
| እርከን 33 | ከ14 አመት- 16 አመት ከ10 ወር | |
| እርከን 34 | ከ15 አመት - 18 አመት | |
| እርከን 35 | ከ16 አመት ከ6 ወር - 19 አመት ከ 6 ወር | |
| እርከን 36 | ከ18 አመት - 21 አመት ከ8 ወር | |
| እርከን 37 | ከ20 አመት - 25 አመት | |
| እርከን 38 | ከእድሜ ልክ እስራት- የሞት ቅጣት | |
| እርከን 39 | የሞት ቅጣት | |

## አባሪ ሁለት

## የገንዘብ መቀጮ ሠንጠረዥ

| የመቀጮ እርከን | የገንዘብ መቀጮው ጣሪያ | |
|---|---|---|
| እርከን 1 | እስከ ብር 1,000.00 | |

www.abyssinialaw.com

| | | |
|---|---|---|
| እርከን 2 | እስከ ብር 2,000.00 | |
| እርከን 3 | እስከ ብር 3,000.00 | |
| እርከን 4 | እስከ ብር 5,000.00 | |
| እርከን 5 | እስከ ብር 7,000.00 | |
| እርከን 6 | እስከ ብር 10,000.00 | |
| እርከን 7 | እስከ ብር 20,000.00 | |
| እርከን 8 | እስከ ብር 30,000.00 | |
| እርከን 9 | እስከ ብር 40,000.00 | |
| እርከን 10 | እስከ ብር 50,000.00 | |
| እርከን 11 | እስከ ብር 75,000.00 | |
| እርከን 12 | እስከ ብር 100,000.00 | |
| እርከን 13 | እስከ ብር 125,000.00 | |
| እርከን 14 | እስከ ብር 150,000.00 | |
| እርከን 15 | እስከ ብር 200,000.00 | |
| እርከን 16 | እስከ ብር 250,000.00 | |
| እርከን 17 | እስከ ብር 300,000.00 | |
| እርከን 18 | እስከ ብር 350,000.00 | |
| እርከን 19 | እስከ ብር 400,000.00 | |
| እርከን 20 | እስከ ብር 500,000.00 | |

www.abyssinialaw.com

| | | |
|---|---|---|
| እርከን 21 | እስከ ብር 1000,000.00 | |
| እርከን 22 | እስከ ብር 2,000,000.00 | |
| እርከን 23 | ከብር 2,000,000 በላይ | |